

ተክሌ ፍሬሰንበት በድሬዳዋ አካባቢ በደርግ ነፈሰገዳዮች በ1970 ዎቹ ከተገደሉት የኢሕኣፓ ኮዋከብት አንዱ

# ኢትዮጵያ

ጥቅምት/ኅዳር 2008 ዓ.ም 3ኛ ዓመት


**ርእስ አንቀጽ ገፅ 2**
የሕዝብ ትግል ሲጎመራ የጠላት ጩኸት ይበረታል

//

**ገፅ 3**

**ዜና ከተባለ**

**ምን ይሰማ....... አገር**

//

**ዜናዎች ገፅ 4**

//

***ትናንትና* ገፅ 5**
በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤የጓድ ቆንጂት ተክሉ ክራሞት

//

**ነጻ ሀሳብ ገፅ 6**
የተዳፈነ እሳት የጠፋ ይመስላል በኢሕአፓ ላይ ዘመቻው ተጧጧፈሳ!
ክፍል 1 & ክፍል 2

//


**የኢትዮጵያ ጋዜጣን በተለያዩ ድረ ገጾች**

**EPRP.COM**
**ASSIMBA.ORG**
**DEBTERAW.COM**
**ETHIOLION.COM**
**ወዘተ.**

- **FACE BOOK (ethiopianewspape**

## አጫጭር ዜናዎች

- የኑሮ ውድነት ግሽበቱ እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው፡፡
- ጂሀዳውያን ናችሁ የተባሉ ክስ ተመሰረተባቸው፡፡
- ከምዕተ ዓመቱ ግቦች ብዙዎቹ በስራ ላይ አልዋሉም ተባለ

- በወገኖቻችን ላይ ግፍ የሚፈጽመው ሳውዲ አረቢያ በአላሙዲ በኩል የሀገራችንን ለም መሬት በርካሽ ገዝቶ እየበዘበዘ ያለው አልበቃ ያለ ይመስል የወያኔ መጋዣ ጠቅላይ ሚኒስቴር በተሰጠው የወያኔ ትዕዛዝ መሰረት ሳውዲ አረቢያ በእርሻው መስክ በበለጠ ስፋት እንድትንቀሳቀስ በይፋ ጋብዟል፤ ተማጥኗል ።
- ድረገጾችን በማፈንና ነጻ የኢንተርኔት ግልጋሎት ላይ ማእቀብ በመጣል የመጥፎ መጥፎ ከተባሉት መንግስታት ውስጥ ወያኔ ከዋና መጥፎዎች (ቻይና፤ኢራን፤ ኩባ) ውስጥ አንዱ ነው ተባለ
- የዘንጋዳ ምርት እየጠፋ በመምጣቱ በወያኔ የፈሉት የቢራ (ማልት) ፋብሪካዎች ኪሳራ እየደረሰብን ነው ሲሉ አማረሩ ።
- ሁለተኛው የኤኮኖሚስት ስብሰባ በሸራተን ሆቴል የተከፈተ ሲሆን በዚሁ ስብሰባ ላይ የተገኘውና ምሁር በሉኝ ባዩ የከሰረው የወያኔው ባለስልጣን አርከበ ዕቁባይ በባንክ አገልግሎት ስራ ባዕዳን እንዳይካፈሉ የተደረገው እገዳ ለመጪው አምስት አመታት ይጸናል በማለት ተናገረ ።
- መብራት ቢጠፋም፤ ግድቡ በዝቶ ተትረፍርፏል ቢባልም፤ በመብራት እጦት የሚሰቃየው ህዝብ ለመብራት የሚከፍለው ዋጋ ግን ይጨምራል ተብሎ ተነገረ ። በሌሎች ሀገሮች የመብራት የውሃ ክፍያ ሆነ የምግብ እህሎችና ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ዋጋ ሲጨምር የሕዝብ አመጽ ሲቀስቀስ ቢታይም ወያኔ ሕዝብን ስለናቀ ያውም በከፋ ችግርና ረሃብ ጊዜ ዋጋ መጨመሩ ዕብሪቱን የሚያሳይ ነው ተብሏል ።
- የደቡብ ሱዳን ዲንካዎች የበዙበት አገዛዝ በተካሄደው ጦርነት ጊዜ ኑዌሮችን ፈጅቶ ስጋቸውን አስበላ ደማቸውን አስጠታ ተብሎ የቀረበው ዘገባ ከእውነት የራቀ ከመሆኑም በላይ ደቡብ ሱዳንና አፍሪካን በአጠቃላይም የሚያዋርድ ነው ተብሎ ተወገዘ ። አማጽያን ኑዌሮችን የሚደግፉ ባዕዳን ያሰራጩትን የሀሰት ክስ የአፍሪካ ህብረትም ማስተጋብቱ ያሳዝናል ያሉ ክፍሎች በሳልቫ ኪር ጦርና በአማጽያኑ ፍጅትና ህጻናትንም መድፈር ቢመዘገብም ይህ በራሱ በቂ አስኮናኝ ድርጊት ሆኖ ሳለ ሰው ገለውና ጠብሰው ዲንካ ወታድሮች በግድ አስበሉ፤ ደም አስጠጡ የሚለው አላስፈላጊና ዘግናኝ ሀሰት ነው ብለዋል ። እንዲያው እውነቱ ተነግሮ ሳያልቅ ሀሰት ፈጠራ ለምን ያስፈልጋል ተብሎም ተተችቷል ።
- የሱዳን የአገር ግዛት ሚኒስቴር በወሰን አካባቢ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ታጣቂዎች “ በገላባትና ሌሎችም አካባቢዎች በርካታ ሱዳኖችን ገደሉ፤አቆሰሉ፤ሰፊ መሬትም ያዙ፤ ለም መሬታችንን ሊዘርፉ ወዘተ.. “ ያለውን በተመለከተ አያ ጅቦ ሳታመካኝ ብላኝ በሚል ታዛቢዎች አጣጥለውታል ። ለም መሬቱን የተቀማው የኢትዮጵያ አርሶ አደር በወራሪ የሱዳን ጦርና ግለሰቦች ላይ የበቀልና የቁጣ እርምጃ ቢወስድ ይገባዋል ያሉ ክፍሎች ሱዳን በገዳሪፍና በሌሎች ቦታዎች ባሉ ሰደተኞች ላይ እንደለመደው የግድያ እርምጃ ይወስዳል የሚል ስጋት አለ ። ወያኔና ሱዳን በጋራ ድንበር ጠባቂ ጦር ማቋቋማቸው አይዘነጋም ::
- በገበያ ላይ ያለው የዕቃዎች ዋጋ ጠዋትና ማታ እጅግ በጣም እየጨመረ በሚሄድበት ሁኔታ የገበያና የገንዘብ ግሽበት የሚጠበቅ ቢሆንም አሁን በሚታየው ሁኔታ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ መድረሱ እየተነገረ ይገኛል፡፡ የብሔራዊ ስታቲስቲክ መሥሪያ ቤት በይፋ ያሳወቀው የመስከረም ወር የግሽበት ቀመር 11.9 ከመቶ ደርሷል የሚል ቢሆንም የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች አስተያየት ግን ከ14 ከመቶ በላይ መሆኑን መረጃ አስደግፈው ያስረዳሉ፡፡ ከስታቲስቲክ መሥሪያ ቤት የሚወጣው ቀመር የወያኔ የፖለቲካ ጫና ስለሚኖርበት ትክክለኛውን አሀዝ እንደማያመለክት ብዙዎች ያውቃሉ፡፡ በዚህ ሳቢያም ዘገባው ተቀባይነት የለውም፡፡ የሆኖ ሆኖ ግሽበቱ እየናረ ችጋሩ በከተማም በገጠርም ሰንጎ የያዘበት ወቅት ነው፡፡ በዚህ ላይ ድርቁ በገበያ ላይ የእህል እጥረት ሊያስከትል እንደሚችልና ያልተጠበቀና ከአሁን ቀደም ያልታየ የዋጋ ንረት ሊከሰት ይችላል የሚል ስጋት ጋርጧል፡፡ የተከሰተው ረሀብ በአጭር ጊዜ ውስጥ አድማሱን እያሰፋ በመሄድ ላይ በመሆኑና የሚያስፈልገው የምግብ አቅርቦት ቀደም ሲል ከተተመነው በላይ በመሆኑ ተጨማሪ የስንዴ ግዢ እንደሚፈጸም ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ ከውጪ ተገዝቶ የሚገባው ስንዴ ከአሁን በፊት አጋጥሞ እንደነበረው እየተዘረፈ በነጋዴዎች እጅ የመግባቱ ስጋት ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ ሳቢያም የእህል ዋጋ ከሚገመተው በላይ ሊንርና ሸማቹን ሕዝብ ሳይቀር ለችጋር ይዳርገዋል ተብሎ ይፈራል፡፡ የወያኔ በምግብ እራስን መቻል ባዶ የፖለቲካ ልፈፋ መዘዙ በቀላሉ ሊታይ እንደማይገባው የወያኔ የጡት ልጆች የሆኑ ጋዜጦች ሳይቀሩ አሳሳቢ መሆኑን እያሰተጋቡ ይገኛሉ፡፡

**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**



# ኢትዮጵያ

በኢሕአፓ የዲሲና አካባቢዉ ደጋፊ አካል
የሚዘጋጅ ወራዊ ጋዜጣ
5309 Georgia Ave. NW 2nd floor Washington DC. 20011
ስ/ቁ፡ 202 291 4217
ኢሜል፡ dc.region.eprp@gmail.com

## ርዕሰ አንቀጽ

## የሕዝብ ትግል ሲጎመራ የጠላት ጩኸት ይበረታል

ተወደደም ተጠላም ፤ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከሁለት አሥርት በላይ የተንሰራፋዉ ዘረኛና አምባገነናዊ አገዛዝ በመሞት ላይ ነዉ ። የአገዛዙ ቁንጮዎችም ሆኑ ለከርሳቸዉ አድረዉ በዙርያቸዉ የተኮለኮሉት ማፈሪያዎች ከእንግዲህ ጀንበራቸዉ በመጥለቅ ላይ ነች። በግብዓተ መሬታቸዉም እንጦርጦስ የሚወርዱበት የታሪክ መቃብር ተቆፍሮ እየጠበቃቸዉ ነዉ ::

ይሁን እንጂ፤ታሪክ በተደጋጋሚ እንዳሳየዉ፤ ማንኛዉም አገዛዝ ሞቱን አሜን ብሎ አይቀበልም ። ይልቁኑ በፍጻሜዉ ሰዓት ዕድሜውን ለማርዘም ሲል፤ በዙርያው የሕዝቡን ጠላቶች አሰባስቦ በማሰለፍ በአልሞት ባይነት ይፍገመገማል። በአገራችን ዉስጥ ዴሞክራሲን ፤ ፍትሕንና እኩልነትን ለማስፈን በመደረግ ላይ ያለዉ ሕዝባዊ ትግል የትናንት ተቀጥላ የመሆኑን ያህል የተከታታይ ትዉልዶችን መሥዋዕት የጠየቀ መሆኑ አይዘነጋም ። በመሆኑም ትግሉን በድሉ አጥቢያ ለመጨፍለቅ ወያኔዎችና የአገዛዛቸዉ ቅምጥሎች ብቻ ሳይሆኑ ባለፉት ጨካኝ ሥርዓቶች ዉስጥ ከሕዝብ ጋር ጥርስ የተናከሱና የደም ዕዳ ያለባቸዉ ኃይሎች ሁሉ እንገፍ እንገፍ ማለታቸዉ ይጠበቃል ። ሁሉም እንደየሥራቸዉ የሚዳኙበትን መጪዉን ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አጥብቀዉ ይፈሩታልና በመሀከላቸዉ ያለዉን ቅራኔ አቻችለዉ በጋራ መዝመት የግድ ይሆንባቸዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሥራዬ ተብሎ የተያዘዉና በተቀነባበረ መልክ በኢሕአፓና በሥሩ ተሰልፎ በታገለዉ ትዉልድ ላይ የሚካሄደዉ ታሪክን የማጠልሸት እንቅስቃሴ የዚሁ ዘመቻ አንድ አካል ነዉ። እንደሚጠበቀዉ ፤ የዘመቻዉ መሪ ወያኔ ሲሆን ፤ ትዉልድ ገዳዮቹ የደርግ ባለሥልጣናትና እጀቻቸዉ በደም የጨቀዩ ፋሺስቶች በአባሪነት አብረዉት በጭቃ ቀቢነት ተሰልፈዋል ። ከነርሱም ሌላ፤ ከአንዱ አገዛዝ ወደሌላዉ በክሽፈት እየተንደባለሉ ለዛሬዉ ዘመን የበቁ ጥቂት ጸጉር ሰንጣቂ “ምሁራን” ሳይቀሩ የክህደት አዳፍኔያቸዉን በኢሕአፓና ከፋሺስቶችና ከዘረኞች ጋር ሲታገሉ በወደቁት ሰማዕቶቻችን ላይ ሲተኩሱ ታይተዋል። በተዘረፈ የሀገር ሀብት ከሞላዉ የወያኔ ካዝና በሚረጭ የገንዘብ ድጎማ የዳጎሰ ጥራዝ ያላቸዉ ታሪክ ደርማሽ ድርሳናት ገበያዉን እያጣበቡት ነዉ ። ጥቁሩ ግራዚያኒ መንግሥቱ ፤ ፍቅረ ሥላሴና ፍስሐ ደስታ “ ደራስያን” ተብለዉ በደም በጠቆረ ቅርሻት ገጾችን አዥጎርጉረዋል ። ነገ ደግሞ የለገሰ አስፋዉ ፤ የመላኩ ተፈራና የሚቹ ዓሊ ሙሳ “ዐይኔን ግንባር ያ’ርገዉ” ማስታወሻዎች በህትመት ተጠርዘዉ መዉጣታቸዉ አይቀርም ። ገንዘብ እስካስገኘለት ድረስ ለመቀበል የማያንገራግር ምግባረ ቢስ አሳታሚ እንደማያጡ ግልጽ ነዉ።

እነዚህን ኃይሎች ከትናንት እስከዛሬ ግንባራችንን ሳናጥፍ ታግለናቸዋል ።ዛሬም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ቆመን እስከዉድቀታቸዉ ዕለት ድረስም እንታገላቸዋለን ። የትናንቶቹ ባለጠመንጃዎች ገድለዉ አልጨረሱንም ፤ አላንበረከኩንምም። የዛሬዎቹ ዘረኛ ባለብረቶች ከቢጤዎቻቸዉ ያልተማሩ ደናቁርት ናቸዉና በዚያዉ የደም መንገድ አብረዋቸዉ ማዝገም ከመረጡ ሀያ አራት ዓመት አልፏቸዋል ። ድርጅታችን ኢሕአፓና በዙሪያዉ የተሰለፉ ታጋዮችም በጽናት ከቆሙበት የመሥዋዕት ጎዳና ለአፍታ እንኳ ዘወር ሳይሉ በመታገል ላይ መሆናቸው በይፋ የሚታወቅ ነዉ ። የጠላቶቹ በትርም ሆነ ታሪክ አጉዳፊ የክህደት ጉድኝታቸዉ ከዓላማዉ ሊያርቀዉ እንዳልቻለ ሁሉ የድሉንም ቀን ከቶ ሊያስቀረዉ አይችልም።

ሕዝባዊዉ ዴሞክራሲያዊ ትግል ያቸንፋል/
በነጻነቷ ኮርታ፤ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር/

## ማን ይሆን በእውነት ሰው?

ከሃማ ቱማ

የሰው ሰውነቱ ምስጢሩ እየጠፋ
ከውልደት ባሻገር ከሰው ነኝ ልፈፋ
አንጎል አለኝ እኔ ከእንስሳ የተለየ
ቆሜ ሂያጅ እኮ ነኝ ስንት ዘመን አለፈ
ከማለት ባሻገር የሰው ሰውነቱ
በምን ይገለፃል የት ላይ ቁምነገሩ
ብለን ብንጠይቅ ምርመራ ቢጀመር
ማነው መልስ የሚሰጥ ማነው የሚናገር?
የሰው ሰውነትን መርምሮ ያወቀ
ማነው ያ ጀግና ሰው በእውነት ሰው የሆነ ?

ጀግና? ይህ መለያ እንዴ ሰውን ሰው የሚያረግ
ዋጋ ሰጪ ፀጋ፤ ከእንስሳ ለይቶ ክብርን የሚሰጥ
ሰው ፈሪ ከሆነ ሰው አይደል የሚለን?
ያ ፈሪ ለእናቱን ሰው አይደል የሚለን?
ወይ ምስጢሩ ሌላ ከቶም ማይጨበጥ
የሰው ሰውነቱ ህልውና ቀበጥ
ከአውሬ ልዩ ስንል እንስሳ የሚያረግ
ከጅብ የሚያስልፍ የእርያ ዘመድ?
የሰው ሰውነቱ በውልደት ከሆነ
ሂትለር ሙሶሎኒ መለስ ያ መንግስቱ
የአውሬ ልጅ ነበሩ ከሴት ሲወለዱ?
ሰውን ሰው ሚያደርገው ምንድነው ምስጢሩ?
ሰው ማነው ሰው ምን ነው አጉል ፍልስፍና
ይናገር ዘረያዕቆብ ወይስ ስፒኖዛ?
ሚሊዮን እያለቀ በረሀብ በአፈና
ሰብዕና ተቀምተን ሀገር ተገንጥላ
ማን ነን ምን ነን ብሎ አጓጉል ምርመራ
ቅንጦት ሳይሆን ቀርቶ አይጠቅሜ ጫጫታ?
ግና! ዘመነ ግሪምቢጥ ቅሉ ድንጋይ ሰብሮ
አውሬ ያልነው ጅብም አህያን አፍቅሮ
ዕድሜ ፀጋን ትቶ መርገምን አንግሶ
ጥቁር ባርያ ሲባል ከነጩ ቤት ገብቶ
ሰው በላው ወያኔ ለአጋር እየታጨ ዴሞክራት ተ
ብሎ
የፈሪ ጦረኛ የቡከን ኮማንደር ምላስ ከመ ጥይት
አውድማ ወረቀት የባዕዱ መድረክ
የባሩዱ ሽታ ታስቦ የሚቀር።፡
በቅማል የሚያርሱ በወሬ ሲነግሱ
የአልፋውንም ቦታ አሜጋ ሲወስደው
የሀገራችን ዜጎች ድንገት ባዳ ሆነው
ያውም ቅኝ ተገዢ እንገንጠል ብለው
መጠየቅ ይነሰን ኢትዮጵያዊ ማነው
መጠየቅ ይብዛብን በእውነት ሰው የቱ ነው?
ወያኔ ወሮበላ አረመኔ ባንዳ
ሲፈጠር ባለጌ ኢትዮጵያን የጠላ
ይሉኝታን ህሊናን በናቅፋ ላይ አንቆ
ደደቢት ቀባሪ ሀፍረትን ጨምሮ
ታዲያ-- ለዚህ አረመኔ ሰው እንዴት ይሰግዳል
ለእንባጮ ታቦት ከመሬት ይደፋል?
ወይስ !ሰው ውርደት ሲቀበል
ፍርሀቱን አቅፎ ቅሌትን ሲቀበል
ገና ከሞት ሳይደርስ አጉል ሲልፈሰፈስ
ሕዝብ--ሀገርን ከድቶ ቃል ኪዳኑን ሲያፈርስ
ያኔ ነው እንበል የሰው ሰውነቱ አፈር የሚለብሰ
ው
በቁሙ የሚሞተው
ከሰው ተርታ ሰፈር ወጥቶ የሚቀረው?
ጀግና ዜጋ ሳይሆን ባንዳ የሚሆነው?
ሀገሩን በሆዱ ተክቶ ሚያመልከው?
ሰው መባላችንም በዚያው የሚያከትመው?
ማን ይሆን በእውነት ሰው !

# ዜና ከተባለ

**መስተዋት ከድሬ**

" በጅል ሰው ከመሳም በብልህ ሰው በጥፊ መመታት ይሻላል "
የኦሮሞ አባባል

ዜና ከተባለ ውጥንቅጡ ብዙ ነው ። ደፍራርሷል--ተስፋንም ይሰጣል ። የሀገራችን ሰው ሳይደፈርስ አይጠራም ብሎ የለ ። አንድ ቀጣፊና ከወደ አንጎሉ ድርቅ ያጠቃው መቶ አለቃ ያለ የሌለውን ውሸት በበርካታ ገጽ ጠቅልሎ ያቀረበው ላይበቃ ከደርጉ ቁንጮች ውስጥ አንዱ የነበረው ፍስሐ ደስታ የተባለው ግለሰብ በበኩሉ ሕዝብን ይቅርታ እጠይቃለሁ እያለ ሞኝ ያለ ይመስል ያንኑ የደርግን የገማ የገለማ ቅጥፈት ጠርዞ አቅርቧል ። የደርግ ውሸቶችን በመጽሐፍ መልክ እየጠቀለለ ሊጭንብን እንደሚሞክረው የሎስ አንጀለሱ "ደርግ አሳታሚዎች" ሰውዬ ሁሉ ከወደ አውስትራሊያም የደርግ ደህንነት መቶ አለቃ የነበረ ሰው ደግሞ በራዲዮ ቃለመጠይቅ በፈረደበት ኢሕአፓ ላይ ያተኮረ ዘመቻውን ለውሱን አድማጮቹ ያስደምጣል። ኦርኬስትራው ኮሾ መሆኑን ማን በነገራቸው!! ወደ ፍስሓ ደስታ ስንመለስ ግን ይህ የፋሺስቱ ደርግ ትልቅ ባለስልጣን በርካታ "እርምጃ ውሰዱ" የሚሉ የማዘዣ ሰነዶችን የፈረመ ነው ። ዘረኛም ስለነበረ ወያኔ እንዳይነካና የደርግን ወታደራዊ ዘመቻ ትኩረቱ በኢሕአፓና በኢዲህ ላይ እንዲሆን ባለው አቅም የጣረ ነው ። በአጭሩ ፍስሃ ደስታ ለሕዝባዊ ፍርድ መቅረብ ያለበት ወንጀለኛ ነው ። ከርችሌ ሳለም ጓድ ይላቸው የነበሩትን ከድቶና ርቆ ለወያኔ ሲሰግድ መቆየቱ እዚያ የነበሩት ነግረውናል ። ፈስሓ ያን ጳፈ ያን ጳፈ በሰጠው ቃል መጠይቅና በኢሕአፓ ላይ በከፈተው ዘመቻ ማንነቱንና ሚናውን ግልጽ አድርጓል ። ለህትመትን ለቃለመጠይቅም የበቃው በዚሁ አቅዋሙ የተነሳ የጻረ ኢሕአፓ ዘመቻ አቀንቃኞች ሊጠቀሙበት ፈልገው መሆኑ ግልጽ ነው ። ፍስሐ ደርግ ያለውን ደብቆ ከነመለስ ዜናዊ የተገናኘ ሲሆን ደርግ ወያኔን በጻረ ኢሕአፓ ዘመቻ ሊደግፍ ሲነሳም አዲግራትና መቀሌ ድረስ መጥቶ የመሳሪያውን ርክክብ የተቆጣጣረ ሰው ነው ። ወደ ለንደን ተጉዞም በዶላር ሰው ሊገዛ የሞከረውም በአመቺው ጊዜ መጋለጥ ያለበት ነው ሲሉ ውስጠ አዋቂዎች ተችተዋል ።

ሌላው መድረክ ይዞ የቆየው ጫጫታ ሻዕቢያን የሚመለከት ነው ። የተባብሩት መንግስታት በሻዕቢያ ላይ ማዕቀቡን አጠናክሮ ይቀጥል ያለ ሲሆን ኢሳያስ የየመን ሁቲ አማጽያንን አሳልፎ ሰጥቶ፤ ሉዓላዊነት ያለውንም አደባይቶ፤በሳውዲና በተባበሩት አረብ ኤሚሬት በርካታ ገንዘብ ስለተከፈለው አሰብንና ሀኒሽ ደሴትን ተጠቀሙበት ብሎ ያስረከበ መሆኑ ተጋልጧል ። ለረዥም ጊዜ የዚህን አምባገነንና የኤርትራን ሕዝብ ያስለቀሰ ጨካኝ መልክ ለማቆንጀት ደፋ ቀና ሲሉ የነበሩትን ስንታዘብ የቆየን ቢሆንም በቅርቡ በዋሺንግተን ያካሄዱት ስብሰባ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ .እንዲሉ ሆኖብናል ። የዚህ ጉባኤ አዘጋጆች ኢትዮጵያውያን ነበሩ ለማለት አያስደፍርም ። ኢትዮጵያን ለግንጠላ የዳረገው ሄርማን ኮሀን፤የወያኔ ዋና አጋር ዴቪድ ሺን፤ ያለፈው ስርዓት ተዋንያን የነበረውና በብዙ ነገሮች የሚጠረጠረው ካሳ ከበደና መሰሎቻቸው ተገኝተው ጸያፍ ንግግር ለሚያደርጉበት ስብሰባ ሀገር ወዳድ ነን የሚሉ ዜጎች ይጠራሉ ብሎ መገመት ከባድ ሆኗል ። ሌላ ካልደመደምን በቀር። ኢሳያስ ለዘመናት ማለት ይቻላል ኢትዮጵያን ሊያፈርስ የጣረ ግለሰብ ሲሆን የሻዕቢያ ጻረ ኢትዮጵያነት ደግሞ መረጃ ጠያቂ አይደለም ። የመቶ ዓመት የቤት ስራ ሰጠኋት ኢትዮጵያን ባዩ ማነው ? ኢሳያስ ኢትዮጵያን ሊገነጠል ካልፈለገ ለምንስ ገንጣዮችን ሲያስተናግድ ሲደግፍ ቆየ? ለምንስ ትላንት ሆነ ዛሬ በህብረ ብሄር ድርጅቶች ላይ ዘመቻን መረጠ? ለምንስ የእነ ኮሎኔል ታደሰን ደብዛ አጠፋ፣ እነ ተስፋዬ ጌታቸውን ገደለ? ለምንስ የማይፈርስ ግንባር መሰረትኩ ብሎ ካስለፈፈ ሳምንት ሳይሞላ ጥምረት ተብዬው የአሸዋ ግንብ ሆነበት? ለምንስ ባለፈው ሳምንት ከኢትዮያ እንገነጠላለን የሚሉትን ኦስሎ ኖርዌይ አሰባስቦ የገንጣይዎች ግንባር እንዲቋቋም አደረገ ? ሻዕቢያ ኢትዮጵያን ሊገነጥል አይፈለግም የሚለው ጻያፍ አነጋጋር ተናጋሪዎቹን በሕዝብ ዘንድ ትዝብት ላይ የሚጥላቸው መሆኑ ግልጽ ነው። መዘባረቅና ወጥ መርገጥ ልማዳቸው የሆኑ ፕሮፌሰር መስፍንም በዚሁ ስብሰባ ራሳቸውን በሁሉ መስክ አጋልጠዋል። ሻዕቢያን ስናውቀው አቆንጅተው ሊያቀርቡልን የሚባክኑት ከንቱዎች ምንኛ ሕዝብን ቢንቁ ነው ሲሉ ታዛቢዎችም ተገርመዋል ። ለማንኛውም ጫጫታውና በምዕራባውያን እየተረጨ ያለው ገንዘብ ሁኔታውን አይቀይረውም ። ያለው ችግር በወያኔና ሻእቢያ እርቅ የሚፈታ አይደለም ። ሁለቱ ቢታረቁ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚተርፈው ዘረኛ ትግራይ ትግሪኚ ጻረ ኢትዮጵያ አገዛዝ ነው ። ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ (የሻዕቢያን ቅጥረኞች አይጠቀልልም) የሚፈልገው የሁለቱን አምባገነን አገዛዞች መንኮታኮትን ነው እንጅ እርቃቸውን አይደለም የሚባለው ። ይህን በተመለከተ የሻዕቢያ ተቃዋሚዎችና ጻረ ወያኔዎች ለማበር ጀምረውት የነበረውን ጥረት ማፋፋምና መቀጠል አለበት ይላሉ የፖለቲካ ተቺዎች ።

ወያኔ ራሱን ይበልጥ ባጋለጠበት ምርጫ ተብዬው መቶ በመቶ አሸነፍኩ ካለ በኋላ የሰብዓዊ መብት ረገጣው በኢትዮጵያ መባባሱን ውስጠ አዋቂዎች አጋልጠዋል ። ተቃዋሚ የተባሉ እንደ በፊቱ ወደ ማዕከላዊና ከርቸሌ መጓዛቸው ቀርቶ በጸጥታ ኃይሎች ይታፈኑና ስየል ተቀብለው ድራሻቸው ይጠፋል ። ባለፉት ወራት የወያኔ አፈና ያተኮረው በጎጃም፤በጎንደር፤ በድሬ ዳዋ፤ ናዝሬት፤ሐረርና ጅማ ነው ተብሏል ። ከሞጣና አርባ ምንጭ የተያዙ ስድስት ዜጎች ደብዛቸው መጥፋቱም ተዘግቧል ።

በከሰረው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ምክንያት ብልሽት ያለው የመካከለኛ ምስራቅና የአፍሪቃ ቀንድ ሁኔታ የባሰ አስጊ እየሆነ መምጣቱን ታዛቢዎችም አስጠንቅቀዋል ። በጅቡቲ የታጠቁ የፍሩድ ድርጅት አማጽያን የገሌህን ጦር እያጠቁ ናቸው ። በሶማሊያ አልሸባብ ደከመ ጠፋ ሲባል ይህ ሀቅ አለመሆኑን ቦንብ እያፈነዳ ያስተባብላል ። የሳውዲና ቃታር ሳላፊስት ዋሃቢስት ዘመቻ ግፊቱ አልቀነሰም ። የጅቡቲውና የሻዕቢያም መሪዎች ቀናቸው አጭር መሆኑን ጠቋሚ ክስተቶች አሉ ። ሴራዎቹም ብዙ ናቸው ። የሱዳኑ በሺርም የነገ ዕጣው ብሩህ አይደለም ። ይህ በዚህ እንዳለ የተባበሩት መንግስታት ጥናት የደቡብ ሱዳን አገዛዝ ከአመጸኞቹ ባልተናነሰ የራሱን ሕዝብ መፍጀቱን፤ሕጻናትን ሳይቀር መጨረሱን አረጋግጦ ከሷል ። ደቡብ ሱዳንን ቦጫቂዎች በዝተዋልና እንደ አንድ ሀገር ለመቆም መቻሏ ውርርድ የሚያስገባ ሆኗል ። መገንጠል መፍትሔ ላለመሆኑ ሌላ ምሳሌ !

አደገ ተመነደገ የሚባለው የወያኔ ኢኮኖሚ ለፈረንጆች እንጂ ለኢትዮጵያውያን ባዕድ መሆኑን ከድህነት መስፋፋቱ፤ከስራአጥነት መብዛቱና ከኑሮ ውድነት ብቻ ሳይሆን ከሚሊዮኖች መራብ ተያይዞ የሚገለጥ ነው ተብሏል ። የረሀብተኛው ቁጥር ከስምንት ሚሊዮን በላይ መድረሱን ወያኔ ራሱ ሊደብቀው አልቻለምና የኢኮኖሚው እድገት አሃዝም ቅጥፈት መሆኑ በሚገባ ተረጋግጧል።

ወ ያ ኔ ተ ጻ ራ ሪ ዎ ቹ ን ለማደናቀፍ፤ለመከፋፈልና ለማጥፋት መድቦት ከነበረው ባጀት ላይ ተጨማሪ 20 ሚሊዮን ብር መጨመሩን የገለጹ ክፍሎች ወያኔ ለማጥቃት ኢላማ ያደረገባቸውን ድርጅቶችና ግለሰቦችም ዝርዝር ቀነስ አድርጎ በቀሪዎቹ ላይ ትኩረቱን ማጠናከሩ ታውቋል ። የሰርጎ ገቦች ቁጥር ንሯል ያሉት ተቺዎች ተቃዋሚዎች ከመቸውም በበለጠ መጠንቀቅ እንዳለባቸው ሲያሥቡ የወያኔ የጡት አባቶችም አገዛዙን ለመርዳት ቅጥረኞቻቸውን በስፋት እያንቀሳቀሱ መሆኑ ይታያል ብለዋል ።

በመጨረሻም ወጣም ወረደም፤ ወያኔዎችም መሰሎቻቸው ጉም ጨበጡም ባከኑም ወያኔ ይሸነፋል። ኢትዮጵያም ነጻ ትወጣለች፤ በጠላቶቿ ሁሉ ላይም ድልን ትቀዳጃለች ሲሉ ጤና ያላቸው ዜጎች ሁሉ ያምናሉ ።

**ጽናቱን ይስጠን ከቆራጥነት ጋር አቀናጅቶ!!**

## ምን ይሰማ……አገር?



**"ወዴት እየሄድን ነዉ ?/"**
(አቶ ክፍሉ ታደሰ መሰሎቹ በጠሩት ጉባዔ ላይ ያቀረበዉ ወረቀት ርዕስ ፤ በጁላይ ፩ የወጣዉ መግለጫቸዉ እንዳሰፈረዉ።)

- **ሰዉዬዉ ለጉዞ ከተነሱ ስንትና ስንት ዓመታት ተቆጥረዋል ። እስከዛሬ ድረስ መድረሻቸዉን አያዉቁትም ማለት ነዉ ?/ .....አጃኢብ ነዉ።**

//

**"አይ አም ሶሪ / ኢሕአፓ የለም ። ...ኢሕአፓ በጭራሽ የለም።"**
(አያሌዉ መርጊያ በአዉስትራሊያዉ የኤስ ቢ ኤስ ሬድዮ ቀርቦ የተናገረዉ ፤ ጁላይ ፲፱ ቀን እንደተደመጠዉ ።)

- **የዘመኑ ብልሃት መቼም እንዲህ ቀላምዶ መጽሐፍ በድርጎ ማሳተም ነዉ ። በአንድ ጎኑም የሐሰተኛ መሃላ ደረት ያሰፋል ይባላል ። ግን የለም የምትሉት ኢሕአፓ ለምን እንዲህ እንቅልፍ ይነሳችኋል ?/**

//

**" ....አንድ የሚገርም ነገር ልንገርህ። የአማራ ክልል የሕዝብ መዝሙር አለ። ይኼ መዝሙር " ለአማራነት ክብር..." የሚል ሐረግ አለዉ። እንግዲህ ያሳይህ፤ ኦሮሞዉም፤ አገዉም በሰልፍ ቆመዉ " ለአማራነት ክብር" እያሉ ይዘምራሉ ።"**
( ዉብሸት ሙላት የተባሉ መምህር ባደረጉት ቃለመጠይቅ የገለጹት። ሪፖርተር ጋዜጣ ነሀሴ ፳ ቀን ፪፻፯ ዓ.ም )

- **ይበልጥ የሚገርመዉ በወያኔዎቹ አገዛዝ አሳሩን ከሚቆጥረዉ ተሳዳጅና ተፈናቃይ የክልሉ ሕዝብ "የአማራነት ክብር ፤" ብሎ የሚዘምር አማራ ከተገኘ አይመስልዎትም መምህር ?**

//

**"..ፕሬዚዳንት አፈወርቂን ብዙ ማለት ይቻላል ፤-ክፉም ፤በጎም ። የኢትዮጵያን መበታተን ይፈልጋል ለሚለኝ ግን ሽንጤን ገትሬ እከራከራለሁ ።"**
( የደርጉ ዲፕሎማት ካሳ ከበደ ፤ በአፍቃሬ ሻቢያ ጉባዔ ላይ ሲናገር የተደመጠ ። ኦክቶበር ፳፫ ቀን ፪፻፲፰ )

- **ለአንድ "የፖለቲካ ቀበሮ የሚገድደዉ የለም ። እንደምትከራከርማ ሞሣዶችም ምስክሮች ናቸዉ ። ....ጥያቄዉ በቀይ ባህር ተሻጋሪዎቹ ተረኞች (ፈላሾች) እነማን ይሆኑ ፤ የድለላዉ ክፍያስ ስንት ይሆን? የሚለዉ ብቻ ነዉ።**

//

**"ኢህአዴግ በሚጠራዉ መድረክ አለመገኘት ማንን ይጠቅማል ?"**
(ግርማ ሠይፉ ማሩ በኢትዮሚድያ ድረገጽ ያስነበቡት መጣጥፍ አቋም ገላጭ ርዕስ፤ ኦክቶበር ፲፫ ፪፻፲፰።)

- **በመገኘትዎ ያገኙትን ጥቅም በመግለጽ ቢጀምሩት አይሻልም ክቡር...(አአ፤ ይቅርታ/ ለካስ "ክቡርነትዎ" ቀርቷልና ) ....አቶ ግርማ ?/ " አሟሟቂ" ነዉ ያለዉ ፤ በፌስ ቡክ መልዕክት የተወልዎት ሰዉ ?/**

ከገጽ 1 የዞረ

- ጂሀዳውያን ናችሁ የተባሉ ክስ ተመሰረተባቸው፡፡ የተወሰኑ ተከሳሾች እራሱን እስላማዊ መንግስት (አይ ሲ ስ) ብሎ የሚጠራው ቡድንን ለመቀላቀል ከ1999 ዓ.ም. ጀምረው በተለየዩ ቦታዎች ሲደራጁ እንደነበር የአቃቤ ህግ ክስ ያትታል፡፡ ተከሳሾቹ "አልኩፋሬ ቢጣጉት" የተሰኘ መፀሐፍ ማንበብ
- ከተከሰሱበት ወንጀል ጋር ተያዥነት እንዳለው ተደርጎ በአቃቤ ህግ ክስ ውስጥ ተካቷል፡፡ በተጨማሪም ተከሳሾቹ የሚከተሉት "ክዋርጂያ" አስተምህሮትን እንደሆነና ከዚህ የተለየ እምነትም በሀገሪቱ ውስጥ መኖር የለበትም የሚል አቋም ይዘው መንቀሳቀሳቸውን አቃቤ ህግ በክሱ ላይ ጠቅሷል፡፡ ተከሳሾቹ አዲስ አበባን የቡድኑ ዋና መቀመጫ አድርገው በወለጋ፣ በሸዋ ሮቢት፣ በሰንበቴ፣ በጅግጅጋ፣ በከሚሴ ይንቀሳቀሱ እንደነበር ክሱ ላይ ተጠቅሷል፡፡ በአጽንኦት የተጠቀሰው የክስ ሀተታ ደግሞ ወያኔን በጦር መሣሪያ ከሥልጣን ለማስወገድ ማሴርና መደራጀት የሚለው ነው፡፡ እራሳቸውን በጦር መሣሪያ
- ለማስታጠቅ ዘረፋ መፈጸም እንደ ስልት አድርገው በዝርፊያ ተሰማርተው እንደነበርም ክሱ ላይ ተወስቷል፡፡ በዚህ የክስ መዝገብ ሃያ ተከሳሾች ማክሰኞ ጥቅምት 16 ቀን 2008ዓ.ም. በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 19ኛ ወንጀል ችሎት ክስ ተመስርቶባቸው ቀርበዋል፡፡ ክሱ ላይ እንደሚያስረዳው ተከሳሾቹ አይ ሲ ስን ለመቀላቀል መሰባሰብ ጀምረዋል በተባለበት ዘመን አይ ሲ ስ ጭራሹን እንዳለተደራጀና ስሙም እንደማይታወቅ መሆኑን አንዳንድ ታዛቢዎች ለዚህ ዘጋቢ ትዝብታቸውን አጋርተውታል፡፡ በሌላ አንጻር ደግሞ የአልሸባብን ተልእኮ ተቀብለው ተንቀሳቅሰዋል የተባሉ አምስት ተከሳሾችም ክስ ተመስርቶባቸው ከላይ በተጠቀሰው ችሎች ቀርበዋል፡፡ ከክሱ መንደርደሪያ መረዳት እንደተቻለው ተከሳሾቹ በሰዓት የተሞሉ ቦምቦችን በኤድና ሞል፣ በማቲ ሞልና በፍሬንድ ሺፕ ህንፃዎች ላይ ለማጥመድ ሲንቀሳቀሱ በክትትል እንደተያዙ ይጠቅሳል፡፡ ተከሳሾቹ የተያዙት 2007 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ሲሆን ክስ ሳይመሰረትባቸው ለምን ከአንድ አመት በላይ እንደቆዩ በአቃቤ ህግ በኩል ምንም የተጠቀሰ የለም፡፡ ወያኔ እንዲህ አይነት ክሶችን የሚያንቀሳቅው የፖለቲካ ውጥረቱን አቅጣጫ ለማስቀየር እንደሆነ የታወቀ መሆኑን የኢትዮጵያን ፖለቲካ እለት ተእለት የሚከታተሉ ተንታኞች ያስረዳሉ፡፡


Rose Unisex Hair Salon (Tsegereda)
6222 Georgia Ave. NW Washington, DC.
20011



የሴቶችንና የወንዶችን፣ የልጆችንና የአዋቂዎችን ፀጉር እናስተካክላለን። ለቀለም ፣ለሹሩባ፣ ለፀጉር ስፌትና ለፐርም ስራ ባለሙያ ከፈለጉ Rose Unisex Hair Salon


- የምዕተ አመት ግቦች ተብለው እንዲተገበሩ ከታቀዱ የልማት እቅዶች መካከል ብዙዎቹ ከወሬ ባለፈ በሥራ ላይ አለመዋላቸው ይፋ ተደረገ፡፡ ወያኔ በጤና፣ በትምህርት፣ በድህነት ቅነሳ፣ በመሰረተ ልማት በተባበሩት መንግስታት የተቀመጠውን በፈረንጆች አቆጣጠር በ2015 ዓ.ም. መቶ በመቶ ሁሉንም ዜጋ ባካተተ ሁኔታ በተግበር መዋል እንደሚገባው ከዛሬ አስራ አምስት አመት በፊት ተቀምጦ የነበረውን መርሀ ግብር እንዲሳካ ሲለፍፍና ሲያስለፍፍ መክረሙ ይታወሳል፡፡ በአሁኑ ወቅት እንኳን እስከ ስምንተኛ ክፍል ያለው ትምህርት ለሁሉም ሊዳረስ ቀርቶ፣ ፊደላትን ያለዩና ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ህጻናትና ጎልማሶች ቁጥር የትዬሌሌ ነው ተብሏል፡፡ በአራት ኪሎ ትምህርት ሚኒስቴር አጥር ዙሪያ ከእናቶቻቸው ጋር በልመና የሚውሉ በጣም በርካታ ህጻናት በርካቶች በሆኑባቸው ሁኔታ ትምህርት ሚንስቴር አጥር ላይ "አንድም ህፃን ከትምህር ቤት ውጪ አይሆንም" የሚል ከመፈክርነቱ ያልዘለለ ተለጥፎ ማየቱ ምጸቱ ያማል፡፡ ወያኔ በግብረ ሰናይ ሥራ ስም ለሆዳቸው ያደሩ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶችንና ሌሎች እንደ ተባበሩት መንግስታት የመሰሉ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥ የሆነ ተግባር ላይ የተሰማሩ ኃላፊዎችን በእከክልኝ ልከክልህ ይትበሀል የሀሰት ዘገባ እንዲቀርብ መደረጉ ያሳዘናቸው ወገኖች ሀቁን እያፈነዱ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ከሁሉም በላይ በወሊድ ጊዜ የሚከሰተው የእናቶች ሞት፣ በእርግዝና ወቅት ሆነ በሴቶች ላይ ጥቃት በሚፈጸምበት ወቅት እንዲሁም በአጠቃላይ ከእናትነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው በሴቶች ላይ የሚደርሱ ህመሞችና ስቃዮች ከመጨመራቸውም አልፎ ዛሬም እንደትናንቱና እንደ ትናንት ወዲያው በቃሬዛ ላይ ሲጓጓዙ ህይወታቸው የሚያልፈው እናቶች ቁጥር ጨምሯል እንጂ አልቀነሰም፡፡ ከዚህ በተረፈም ለህክምና የሚወጣው ወጪ ከዘጠና ከመቶ በላይ ከሚሆነው ሕዝብ አቅም በላይ በመሆኑ በየጎጆው የስቃይ ድምጽ እያሰማ የሚሞተው ሰው በዛ እንጂ አልቀነሰም፡፡ መድሀኒት እጅግ በጣም ውድ ነው፡፡ የመጠቀም ዘመናቸው ያለፉ መድሀኒቶች በገበያ ላይ ፈሰዋል፡፡ የእናቶችን ሞት በተመለከተ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጥቅምት 11 ቀን 2008 ዓ.ም. በአፍሪካ ኤኮኖሚክ ኮሚሽን አዳራሽ በተካሄደው ስብሰባ ላይ በይፋ ተነግሯል፡፡ የወያኔ ተወካዮች አሀዝ እየደረደሩ ለመሟገት ያደረጉት ጥረት ከዋዛ ፈዛዛነት የዘለለ ሊሆን አልቻለም፡፡ ወያኔ ለፖለቲካ ተረፌታ "ድህነት ታሪክ " ይሆናል እያለ ቢለፍፍም መሬት ላይ ያለው ሀቅ ግን አፈር አልብሰው ሊሸፍኑት የማይቻል ነው፡፡ በስብሰባው ላይ 22.6 ሚሊዮን የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአስከፊ ድህነት ውስጥ የሚገኝ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ይህ አገላለጽ ወያኔን ለመጥቀም ሆን ተብሎ ወረድ እንደተደረገ የፖለቲካዊ ኤኮኖሚ አዋቂዎች ይተቻሉ፡፡ በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ከመቶ ሚሊዮን እንደዘለለ እየታወቀ አንድ አራተኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ከድህነት ወለል በታች በሆነ ኑሮ እንደሚማቅቅ የቀረበውን ሀቁ በግልባጩ እንደሆነና ሦስት አራተኛው ማለትም 75 ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝብ እጅግ ዘግናኝ በሆነ የድህነት ሁኔታ ውስጥ እንደሚማቅቅ ለሀቅ የቆሙ የምጣኔ ሀብት ምሁራን በአንክሮ ያስረዳሉ፡፡ተጨማሪ በጤና በኩል በወያኔ አፈቀላጤዎች በተደጋጋሚ የኤች አይ ቪ ኤድስን ስርጭት መቀነስ መቻሉ ቢጠቀስም እራሳቸውን ከማታለል በላይ ያለፈ እንደማይሆን በርካቶች ትዝብታቸውን ይሰነዝራሉ፡፡ በአደንዛዥ እጾችና በአልኮሆል ሱሰኝነት የሚጠመደው ሕዝብ በተለይ ደግሞ ለአገሩና ለወገኑ ብዙ የሚጠበቅበት ወጣቱ በአስከፊ ሁኔታ እየተጠቃ ባለበትና የእርቃን ዳንኪራ ቤቶች በበረከቱበት ኤች አይ ቪ ማለትም ኤይድስ በእጥፍ ይጨምራል እንጂ አይቀንስም፡፡ በሳምባና በጉበት በሽታ የሚሰቃየው ሕዝብ ቁጥርም በአስደንጋጭ ሁኔታ እየናረ በመሄድ ላይ ለመሆኑ በህክምና ላይ የሚሠሩ ባለሙያዎች ይጠቅሳሉ፡፡ የጉበት በሽታ በአሁኑ ወቅት ቀዳሚ ነፍሰ ገዳይ በሽታ እየሆነ መምጣቱን እነዚሁ ወገኖች በቅሬታ ሀሳባቸውን ይሰነዝራሉ፡፡ ይህን ሁኔታ በተመለከተ ወያኔ የሀሰት የእድገት አሀዝ እንደሚደረድረው "የሚሊየሙን ግብ መታሁ" እያለ በየስብሰባው የሚያቀርበው የአሀዝ ድርደራ ውሀ የማይቋጥር መሆኑን የፖለቲካ ተንታኞች ያቀርቡና ለኢትዮጵያ በጎ የሆኑ ተግባራት በወያኔ መቃብር ላይ እንጂ በወያኔ ሊፈጸሙ ከቶውንም እንደማይችሉ በአጽንኦት ያስረዳሉ፡፡


ከኢሕኣፓ ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

ስልክ፡ (202) 291-4217
ኢሜል፡ espic@aol.com
ፖስታ፡ EPRP
P.O. Box 73337
Washington, DC. 20056
ድረ ገጽ፡ eprp.com

ፍኖተ ዴሞክራሲን ለማዳመጥ Finote.org

ከኢሕኣፓ ወክንድ (EPRPYL) ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

ስልክ፡ (202) 291-5832
ኢሜል፡ eprpylnew@gmail.com
ፖስታ፡ EPRPYL
5309 Georgia ave.
Washington, DC. 20011
ድረ ገጽ፡ eprpyl.com

ካለፈዉ የቀተለ

## በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤ የጓድ ቆንጂት ተክሉ ክራሞት

### ፯

አሳሾቹ መላዉን አዲስ አበባ በአንድ ቀን ለማዳረስ የሚያበቃ ችሎታ ባይኖራቸዉም ይህን ድክመታቸዉን ግን በሌሎች ዘዴዎች ሊያካክሱት ችለዋል ። በሕዝቡ ልቡና የተሰነቀሩትን ፍርሀቶች በመመርኮዝ ፤ በመቶዎቹ በሚቆጠር ሜትር ጥልቀት መሬት ዉስጥ የተቀበሩ ብረታ ብረቶችን መርምሮ ማግኘት የሚችል ልዩ መሣሪያ ያላቸዉ መሆኑን አስነገሩ ። ይኼዉ ዘዴያቸዉ ሰመረና በርካታ ተላላዎች ፤ ተዓምረኛዉን መሣሪያ ቀድመው ፤ የቀበሯቸዉን የጦር መሣርያዎችና ጥይቶች አዉጥተዉ በመያዝ ወደየፖሊስ ጣቢያዎቹና ወደየቀበሌ ጽ/ቤቶቹ ተንጋጉ ።

አሰሳዉ በተጀመረ በሁለተኛዉ ቀን ከቀትር በኋላ ረፋዱ ላይ አሳሾቹ ወደ እኛ ቤት መጡ ። በዚያን ጊዜ ግን ዘመቻዉ በስሜት ላይ ያስከተለዉ ዉጥረትና ጫና እንደ መጀመሪያዉ ቀን ሳይሆን ሟሽሾ ነበር ። አሳሾቹ በቀደመዉ ቀን አሰሳቸዉ አንድም ፤ እጅግ በርካታ የጦር መሣሪያዎችን በመዉረሳቸዉ ፤ አንድም ከመሪዎቻችን አንዱ የሆነዉ ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ በአንድ ባንዳ ከተጠቆመበት በኋላ ከሰባተኛ ፎቅ ራሱን ወርዉሮ ሕይወቱን ለማጥፋት በመገደዱ ሳቢያ የረኩ ይመስሉ ነበር ። ከዚህም ሌላ አሳሾቹ ተዳክመዉም ተሰላችተዉም ነበር ። ብቻዬን በነበርኩበት ሰዓት አምስት ሆነዉ ወደ ቤታችን መጡ ። ወደ ዉስጥ ከአስገባኋቸዉ በኋላ የተለመዱትን ጥያቄዎቻቸዉን አላዋቂነቴን በሚያመላክት መንገድ እየመለስኩ ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላኛዉ እየመራሁ ወሰድኳቸዉ ። ፍተሻዉ በአምስት ደቂቃ ዉስጥ ተጠናቀቀ ። ከሦስት ቀናት በኋላ ወደ ተለመደዉ ተግባራችን ተሰማራን ። የግንኙነት መሥመሮችን መልሰን መዘርጋት ፤ ተበታኝ ወረቀቶችን፤ መፈክሮችንና ፖስተሮችን ማተም ፤ ድርጅታዊና የቅስቀሳ ሥራዎቻችንን ማከናወን ቀጠልን ።

አሰሳዉና የመንጥር ዘመቻዉ እንቅስቃሴዎቻችንን ያላስቆመና ያላዳከመ መሆኑን አገዛዙ ተገነዘበ ። በመሆኑም እመቃዉ ተጠናክሮ ቀጠለ ። ሰዎችን አፍኖ መዉሰድ በይበልጥ ተስፋፋ ። ግድያዎችና ስየሎች በሰፊዉ የተያዙ የተለምዶ ተግባራት ሆኑ ። "እንደ መብረቅ ፈጣን" የሆኑና ስለጭካኔያቸዉ ብዙ የተወራላቸዉ ''ችግር አስወጋጅ" ኃይሎች በከተማዉ ዳር እስከዳር ተሰማሩ ። እነዚሁ ኃይሎች ወደርየለሽ ጭካኔያቸዉን በ፲፱፻፷፰ቱ (አሥራ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ስምንት ዓ.ም ) የዓለም ላብ አደሮች ቀን ዋዜማ ላይ በተግባር አስመስከሩ ።

በበዓሉ ዋዜማ ላይ ላብ አደሮች ፤ ወጣቶች ፤ ሴቶችና የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ዕለቱን የራሳቸዉ በሆነ መንገድ ለማክበር በአዲስ አበባ የዉስጥ መንገዶች የተቃዉሞ ስብሰባዎችንና ሰልፎችን በማድረግ ላይ ነበሩ ። ሽብርን በመዝራት ጠቅላላዉን ሕዝብ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በፍርሀት ለማራድ የአገዛዙ ታጣቂ ወሮበሎች ፤ወታደሮችና የደኅንነት ሠራተኞች የዋሁን የተቃዉሞ ሰልፈኛ ለወሬ ነጋሪ ሳይተርፍ ለመጨፍጨፍ ፤ ለጅምላ ፍጅት ተሰማሩ ።በዚያ የተረገመ ምሽት በሺህዎች የሚቆጠሩ (ዝቅተኛዉ ግምት ሁለት ሺህ አድርጎታል ፤)ተገድለዉ በፍሳሽ መዉረጃ ጉድጓዶች ዉስጥ፤ ከድልድዮች ሥር ፤ ... ወዘተ...ተጥለዋል ። ይህንን ግብረ ሽብርና ግድያ ተከትሎ ፤ ከመሀከላችን የጓዶች ሕይወት የተቀጠፈበት ሁለተኛዉ የቤት ለቤት አሰሳ ከአራት ቀናት በኋላተጀመረ ።

የህቡዕ ሕይወቴ ዕለታዊ ዉሎ ይበልጡኑ አስቸጋሪና ፈታኝ እየሆነ ሄደ ። በእያንዳንዱ ቀን አስር ወይም አስራ ሁለት ድርጅታዊ ቀጠሮዎች ላይ መገኘት ይጠበቅብኛል ። እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ደግሞ የየራሱን ዝንፍ የሌለበትስልት ፤ ከፍተኛ ጥንቃቄ ፤ ዲሲፕሊንና ፈጠራ ይጠይቃል ። የህቡዕ እንቅስቃሴ የአንድ ሰዉ የብቃት ልክ የሚፈተንበት የመሆኑን ያህል የችሎታዎቹንም ድንበር ያስፋፋለታል ። በበርካታ የጥናት ቡድኖች ዉስጥ እና ደፋርነትን በሚጠይቁ አያሌ የተግባር እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳትፌአለሁ ። አቅልሞ ማተምን የመሳሰሉት ተግባራት በጣሙን ይቀልሉኝ ነበር ። ማንኛዉንም ሻካራነት የሌለዉን የቁስ ገጽ ፤ የማባዣ ካርቦን (ስቴንስል ) እና ቀለም በመጠቀም ፤ ታትመዉ የሚሰራጩ ነገሮችን ሁሉ በተፈለገዉ ቁጥር ማባዛት እንደሚቻለኝ በሂደት ተረድቼዋለሁ ። ለሕትመት ዝግጅት የሚያስፈልጉትም መሳሪያዎች ለአጠቃቀም የማያስቸግሩና በቀላሉ ሊደበቁ የሚችሉ ናቸዉ ። ስምንት ኢንች ወርድና አሥራ አንድ ኢንች ቁመት ያለዉ አንድ መስተዋት ፤ የፎቶግራፍ መስቀያ (ማዕቀፍ) ፤ የምግብ ጠረጴዛ ወይም ከፎርማይካ የተሠራ የአልጋ ራስጌ ሳንቃ ፤ ወዘተ...በቂ ናቸዉ ። እነዚህ መሳሪያዎች ደግሞ በማንኛዉም የመኖርያ ቤት የሚገኙ እንደመሆናቸዉ ከተለምዶ መስመር ወጥተዉ ለጥርጣሬ የሚያበቁ አይደሉም ።

የአገዛዙ እመቃ እየበረታ በሄደ ቁጥር ፤ የመጋለጡና የመታሠሩ አደጋ ሊያጋጥም የሚችል ሆኖ እየቀረበ ሄደ ። በእያንዳንዱ ቀን አደጋ ዉስጥ የመዉደቁ ዕድል ይበልጡን እያፈጠጠ መጣ ። በየቀኑ የቅርብ ጓደኛዬ ወይም ከማዉቃቸዉ ሰዎች አንዱ ህቡዕ ይገባል ፤ ወይም ይታሰራል ፤ ታፍኖ ይያዛል ፤ ይቆስላል ፤ አልያም ይሠዋል ። የዚያኑ ያህልም የአገዛዙን እመቃ የመቋቋም - የመጋተሩ ፍልሚያ አያደገ ነበር ።ቀድሞዉንም ቢሆን ህቡዕ ለመግባትም ሆነ ዐመጽን በዐመጽ ለመጋተር የተገደድነዉ በፋሺስታዊዉ መንግሥት እመቃ ተገፍተን መሆኑ መጤን አለበት ። ብዙዉን ጊዜ የተኩስ ልዉዉጦች ይካሄዳሉ ። በቁጥርም ሆነ በትጥቅ ብልጫ ካለዉ ጠላት ጋር ጓዶቻችን እስከመጨረሻይቱ ቅጽበት የሚያደርጓቸዉ የጀግንነት ትንቅንቆች የሕዝቡን መንፈስ ሲያነቃቁት በኛም ልቡና በትግሉ እንድንገፋ ፍላጎትንና ጥንካሬን አስርጸዋል ። ሰማዕትነታቸዉ በሕዝባችን ታሪክ ዉስጥ አዲስ ምዕራፍ አንጥቧል ። ይህ በራሱ፤ በሰማዕትነት የፈሰሰዉ ደም ከደረቀ በኋላ በሕዝቡ ልብ ለረዥም ጊዜ ሲታወስ የሚኖር ታላቅ ድል ነዉ ።

## ትናንትና

አብዛኛዎቹ ጓዶች ምሳሌነት ያለዉ ወኔና ጽናትን አሳይተዋል ። ለዓላማ ራስን የማስገዛትን ትርጓሜ ፤ እንዲሁም የሀገርንና የሕዝብን ፍቅር ምንነት በተግባር መስክረዋል ። በጥብቅ ሥነምግባር የታነጹ የመሆናቸዉን ያህል ለሕዝብ የነበራቸዉን ፍቅር ጥብቀት ያህል ለበሰበሰዉ ኢ-ሰብዐዊ ሥርዓት የነበራቸዉ ጥላቻ ወሰን አልነበረዉም ። የግፈኞችን ስየል ሥቃይ ተቋቁም ለማለፍ ያስቻላቸዉ ቁርጠኛነት ከነበራቸዉ ጥብቅ እምነት የመነጨ ነዉ ። ብዙዎቹ ድርጅታቸዉንና ድርጅታዊ ምስጢሮችን ለጠላት አሳልፈዉ ላለመስጠት ሲሉ ሕይወታቸዉን በገዛ እጃቸዉ አጥፍተዋል ። ሕዝባዊ ጀግኖች ተፈጥረዋል ፤ .....ቆራጥ ጀግኖችም ተከስተዋል ፤ .....አገሪቱም ክስተቱን አስተዉላዋለች ። ይህም ለዓላማ መሞትንና ለአገር መሠዋትን የመሰለ የቆራጥነት አስተምህሮ ለትዉልድ ለማስተላለፍ የበቃ ተጨማሪ ድል ነበር ።

ይሁን እንጂ ፤ አያት ቅድመ አያቶቻችን እንደሚሉት ፤ " የእናት ሆድ ዝንጉርጉር ፤" መሆኑ አልቀረም ። ጀግኖችና ቡከኖች የመኖራቸዉን ያህል ፤ ከሀዲዎችና ተቃራኒዎቻቸዉም አሉ ። ሁላችንም የሰዉ ፍጡር በመሆናችን ሥጋችን ደካማ ነዉና በአስከፊዉ ስየል ሥቃይ ጥንካሬያቸዉ ተሰብሮ ድርጅታቸዉን ለአደጋ ያጋለጡ ጥቂቶች አልታጡም ።በዚህ መልኩ የተበላ አንድ ጓድ ወይም አንድ ዲሞክራት ደግሞ ለበርካታ አባላት እስራት መንስዔ መሆኑ የማይቀር ነዉ ። ይህን የመሰለዉን አጉል ዕጣ ለማስቀረት ሲባል አንድ ጓድ ገጽታ በመለወጥ ዘዴ የተካነ መሆን የሚገባዉ ሲሆን እጅግ አስፈላጊ ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ ከሌሎች ጓዶች ጋር የሚያደርጋቸዉን ግንኙነቶች ማቀብ ይኖርበታል ። ከዚህም በተጨማሪ የተለምዶ ተግባራትን የማስወገድ ልምድ ሊያዳብር ይገባዋል ፤...የመገናኛና የቀጠሮ ሥፍራዎችን ፤ የሚጠቀሙባቸዉን የሕዝብ ስልኮች ፤ ምስጢራዊ ስያሜዎችና የይለፍ ቃላት አዘዉትሮ መለወጥና ማፈራረቅ ፤አንዳንድ ጊዜም በኛ ጓዶች ዘንድ ሳይቀር ጠቀሜታቸዉ የቀረ መስሎ እስኪገመት ድረስ በከፍተኛ ምስጢርነት መያዝ ያስፈልጋል ።

የመገናኛ ሥፍራዎችን በሚመለከት ፤በጠላት ወጥመድ ዉስጥ ላለመዉደቅና ከመረጃ ሠራተኞች ክትትል ለመዳን፤ እጅግ በጣም ጥንቁቅ ፤ አስተዋይ ፤ አካባቢዉን በሚመለከትም በቂ መረጃ የታጠቅን መሆን የግድ ነበረብን። እያንዳንዱ ጓድ የደርግን የመረጃ አነፍናፊዎች እንደምን ማወቅና ከክትትላቸዉም እንደምን ማምለጥ እንደሚቻል ፤ እንዲሁም ራስን ከአካባቢ ጋር በማዋሃድ ከጠላት ዕይታ የመሰወርን ዘዴ አስቸጋሪ ተግባራዊ ልምምዶችን በማድረግ መማር ነበረበት።

በተለምዶአዊዉ ዕለታዊ ሁነቶችና ድርጊቶች ዉስጥ ጥቃቅንና ዝርዝር ለሆኑ ጉዳዮች ተገቢዉን ትኩረት ባለመስጠቴ ሳቢያ ከአደጋ አፋፍ የደረስኩበት አንድ ወቅት ትዝ ይለኛል ።በአንድ ቤተክርስቲያን ዉስጥ ከሌሎች ሴቶች ጋር የተለመደዉን ስብሰባ አካሄድ ነበር ። እዚያ በምደርስበት ጊዜ ሁሉ በቤተክርስትያኑ አንድ ወገን በርካታ ሴቶች ተሰባስበዉ እመለከት ነበር ።በዚህም የተነሳ እኔና የተቀሩት ጓዶቼ ሰዉ እምብዛም ወደማይበዛበት ወገን በመሄድ ቤተክርስትያኑን ከተሳለምን በኋላ በቀጥታ ለዕለቱ መነጋገሪያችን ወደሆነዉ አጀንዳ በማምራት እንወያያለን ። በመቀጠልም እያንዳንዳችን በያዝነዉ ቅርጫት ዉስጥ ያመጣናቸዉን ተበታኝ ወረቀቶች ወይም የተለያዩ ድርጅታዊ ጽሁፎችን እንለዋወጣለን ። ከዕለታት በአንዱ ቀን ፤ በርከት ብለዉ ከተሰበሰቡት ሴቶች መሀከል አንዷ ወደ እኔ መጥታ ለምን ለወንዶች ብቻ በተመደበዉ ሥፍራ እንደምንሳለም እስክትጠይቀኝ ድረስ፤ የቤተክርስትያኑ አንድ ወገን ጭር ሲል ሌላዉ ለምን ሰዉ እንደሚበዛበት ቁም ነገሬ ብዬ አላሰብኩበትም ነበር ። ሴትየዋ ከዚህ ሌላ እንደሌሎቹ ምዕመናን አንገቴ ላይ ማተብ የሌለኝ መሆኑን ታዝባ ነበርና ጥርጣሬ ገብቷታል። "አንገትሽ ላይ ክር ላለማሰር የሚያበቃሽን ያህል የዘመንሽ አትመስይም ፤" በማለት ህጸጽ ያለችዉን ታዥጎደጉድብኝ ጀመር ። " ሴቶች የት ጋ እንደሚጸልዩም ሆነ የተለየ የመግቢያ በር እንደሚጠቀሙ አታዉቂም ። በዚያ ላይ ደግሞ በቅዳሴ ሰዓት የሚደወሉትን የተለያዩ የመረዋ ድምጾች አታዉቂአቸዉም ።" አጥርቶ መስማት የሚሳነኝ ጅላንፎ መስሎ ለመታየት እየሞከርኩ ጆሮ ነፈግኋት ። ከዚያ በፊት በተለያየ ጊዜ ከጓዶቼ ጋር ሳወራ ደጋግማ አይታኝ ነበርና ሙከራዬ በፍጹም አላሳመናትም።

ሴትዮይቱ ወደ ቤተክርስትያኑ ባለሥልጣናት በመሄድ ስለ" ጸጉረ ልዉጦቹ" ሴቶች ለማሳወቅ ፈልጋ የነበረ ሲሆን ያንን ከማድረጓ አስቀድመን ሥፍራዉን ለቅቀን ሄድን ። ዳግመኛም ወደዚያ ቤተክርስትያን አልተመለስንም። ከዚያ አጋጣሚ በኋላ አብያተ ክርስትያናትን ለስብሰባ አዘዉትሬ መጠቀሜን ተዉኩት። ዘግይቼ እንደተረዳሁት ፤ የአጥር መግቢያ የሌላቸዉ የበር መዝጊያ እንዲያስገጥሙ ፤ ከእሁድና ከታቦት የንግሥ ቀናት በስተቀር በሮቻቸዉን እንዲቆልፉ የሚያስገድድ ማዘዣ ለአብያተ ክርስትያናቱ ተላልፎ ነበር ። ያም ሆነ ይህ ከዚያች ቀን አንስቶ ጥቃቅን ለሚመስሉ ዝርዝር ሁነቶች ሳይቀር ተገቢ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ በይበልጥ ተገነዘብኩኝ ።

ይቀጥላል........

# ነጻ ሀሳብ

## የተዳፈነ እሳት የጠፋ ይመስላል
## በኢሕአፓ ላይ ዘመቻው ተጧጧፈሳ!

**ክፍል 1**

ኢሕ አፓ ጠፍቷል፤ተኗል፤ ሞቷል በሚል ደርግና አችከሮቹ ይደነፉ በነበረበት ወቅት እሳተ ገሞራው ሐይሉ ገብረ ዮሓንስ የምትቀጥለውን በ 1983 " እሳት ጠፋ! ይበል? በሚል ርዕስ ከትቦልን ነበር፤

*ስንቱን ፈተና አልፎ በሚይስደንቅ ትግሥት*
*በትግሉ ድቁና ሆነ ቅስና፤ኋላም በምንኩስናው ዘመናት*
*ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ሲዘጋጅ ለብቃት*
*ዛሬ ቢያወሩልኝ አልሰማም የሸገተ ወሬ የቀመለ*
*ድፍን አበሻ ቢቀላምድ እንዲህ እንዲህ እያለ*
*ገዳሙን ትቶ ኮበለለ*
*"ይህ አባ ቆቡን ጣለ !!"*

ኢህአፓም ትግሉን ቶት አልከሰመ፤ ገሞራውም በሆድ አምላኪዎችና ፈሪዎች ቢከዳም እስከ ዕለት ሞቱ ጻረ ወያኔ ትግሉን አላቆመ ። እሳት አልጠፋ አለና ታዲያ የደርጉ ሲያበቃ የወያኔ ዘረኛ ሰደድ አሁንም በኢሕአፓ ላይ ተነሳ ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ጻረ ኢሕአፓው ዘመቻ በየቦታው ተፋፍሟል ። ለምን ብሎ መጠየቅ ራሱ የለም ተብዬው ድርጅት ለወያኔ ውጋት ሆኖ መቀጠሉን አብሳሪ ነው ። ወያኔ ከየህጋዊ ድርጅቶች ኢሕአፓ ያላቸውን እየመነጠረ መቀጠሉ ደግሞ ምስጢር አይደለም ። በአሁኑ ጊዜ ጠንክሮ የመጣው ዘመቻ በሀገር ቤትም ከውጭ ሀገርም ነው ። ከአሜሪካና አውሮጳ ወደ ሀገር ቤት እየደወሉና ገንዘብ ሞልቷልና ገላ ሰደው ለሰዓቶች የሚያወሩት የወያኔ አዳናቂዎች በኢሕ አፓና በአመራሩ ላይ ሰፊ ሀሰትን እያሰራጬ ናቸው ። ውሸትን በተመለከተ ገሞራው በዚሁ የግጥም መጽሃፉ የሚከተለውን አስፍሮ ነበርና መጥቀሱ ጠቀሜታ አለው ።

" ነገረ-ውሸት በዓለም አቀፍ ደረጃ ጭምር የሚያውደለድል ችግር እንደ መሆኑ በዘመናችን የነገር ልቦና (ሳይኮሎጂስቶች) ምሁራን እንዳጦዘ አለ ። የነገረ ሐሰትን ውስብስብ ባህርይና የመነሻው ጥቅንጥቁንም ሊመረምሩት በተነሱ ቁጥር የራሳቸውንም አዕምሮ ሳይቀር እንዳናወዘው አለ ። ሀሰት በጊዜ ይዘት አንጻር ስሉስ ወቅቶችንም ይጠቀምባቸዋል ። በመሆኑም የጊዜ ገደብ አያውቅም። በሬ ወልዶ ነበር፤ በሬ እየወለደ ነው ፤ በሬ ይወልዳል በሚል የቱልቱላ ጥሩምባው ስላለፈው ይወሸክታል ። ባሁኑም ጣቃውን ይቀዳል፤ በወድፊቱም ላይ ይቀጥፋል ። ውሸት በሁለንተናው ጻረ ሀቅ ነው ። በግለሰቦችም ሆነ በማህበረሰቦች ኑሮ ውስጥ የድክመት ሸንቁር ቀዳዳ ፈልጎ በመግባት አለያም ለስላሳ የህይወት ክፍሎችን ሰርስሮና ሰርጎ በመግባት ያላፈረሰው ትዳር፤ ያልናደው ንብረት፤ያልመዘበረው ወዳጅነት አይገኝም ።ሌላው ቀርቶ እንደ ፍቅር ባለው ትልቅ የስሜት ወዳጃዊ ግንኙነቶች ውስጥ ጣልቃ ገብቶ ሱክ በማለት፤ ፍቅረኞችን ጭምር ሲያናቁር ኖሯል። ልባዊ ዝምድናን ፈጥረው ትዳርን ያህል ባለቃል ኪዳን ውል መስርተው፤ ንብረት አደርጅተው፤ወልደው፤ ከብደው ለዘመናት ተከባብረው የኖሩ አባት እናቶችን ሳይቀር ውሸት በመሃላቸው ገብቶ በማናወጽ የሞቀ ትዳራቸውን በማተራመስ እንዳልነበር ሲያደርገው በተደጋጋሚ ታይቷል ። በዚህ አጸያፊ ተግባሩ በየማህበረሰቡ አባላት ሁሉ ርኩስ ውሸት ሲወገዝና ሲኮነን ኖሯል ።"

ቢወገዝ ቢከሰስም ውሸት ተነቃብኝ ብሎ የሚተን ሳይሆን ራሱን በመደጋገም ሃቅን መስሎ ሊያወናብድ ይጥራል ። ውሸታችሁ ተነቅቶበታል በቃ ሲባሉ እምቢኝ አሻፈረን ብለው የደረቁ ወያኔዎችና የደርግ ርዝራዦችን ዛሬ ይመለከቷል፡ ገሞራው ትንተናውን በመቀጠል የሚከተለውን አስፍሮ ነበር ።

" በየፖለቲካው መስክ የሚቧረቅ ውሸት የራሱ ዓይነትና ይዞታው ባህርይ ሲኖረው በአብዛኛው ሥልጣንና ሃይላዊ ጉልበት ላይ በማነፋነፍ የሚሽከረከር ውሸት ነው ። ለሥልጣን የሚቋምጥ ግለ-ሰብ ወይም ቡድን "ከእኔ በላይ ለአሳር ነው" በሚል ዘዴ "ከሰማይት የወረድኩ ልዩ ፍጡር ነኝ" እስከማለት ድረስ ያስቀባጥረዋል ።ከመሰሉ ፍጡርም የተለየ ልዩ ሰው ለመምሰል " ደሜ ሐምራዊ ነው " ብሎ እስከመዘላበድ ድረስ ያቃዠዋል ።ትውልዴም ባለ ሺ ጅማት ካላቸው ከነእንቶኔ ዝርያ፤ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው እስከማለትም ድረስ ያስቀላምደዋል ። ለዚህ ዓይነት የባለ ውሸት አበጋዝ ብዙ ስመ ጥርና ዕውቅ አምባገኖችን በናሙናነት ማቅረብ ይቻላል።...ትንሽ ዘርዘር አድርገን በዘመናችን የሚከናወኑትን ዓይን አውጣ ውሸቶችን ብንጠቃቅስ ከፖለቲካ ጋር የቅርብ ዝምድና ያለውን የፕሮፓጋንዳ ውሸት መጥቀሱ እጅግ አርኪ ነው ። ባልነበረ ጦር ሜዳና ባልዘመተ ሰራዊት ባዶ ሁኔታ ላይ የድል ቅዠት ያወፈፈው ቡድን ድንገት ተነስቶ ሺ ሰዎች ማረከሁ፤ዘመናይ መሳሪያዎችን በገፍ ማረከሁ፤ሺ ገደልኩ፤ ጉጡርጡራ የተባለውን ልዩ ለጦርነት አመቺ ቦታ ከጠላት አስለቅቄ ከእጄ አገባሁ በማለት ደረቅ ቱልቱላውን ይነፋል ።የሚገርመው ደግሞ የራሱ ተዋጊዎች ልዩ የአቅቤ ርዕስ ጥይት የማያስመታ መድሃኒትና አስማት ያላቸው ይመስል ከዚህ ሁሉ ወራሪ ሰራዊት ውስጥ ያን ያህል ከፍተኛሲያደርግ አንድ እንኳን መሞት ቀርቶ ያልቆሰለበት መሆኑን አለመግለጹ ነው ። ይህ ዓይነት የጦርነት ግብግብ ውሸት በዘመኑ ቋንቋ ጸሊም ፕሮፓጋንዳ ወይም አሳሳች ዜና ተብሎ ይጠራል።አስር ተዋጊዎችን ምርኮ አስገብቶ እንደሆነ አስሩን በአስር ያባዛና፤መቶ ተዋጊዎች ማርኬያለሁ ሲል ይፋሽካል። የትልቅ ከተማ ጎረቤት የሆነች የገጠር መንደር የያዘ እንደሆነ ዋናውን ከተማ በቁጥጥሬ ስር አድርጊያለሁ ሲል ጣቃውን ይቀዳል ። ከዋሹ አይቀር እንዲህ ቅልጥልጥ ብሎ እንጂ! በተራ ጆሮዎች በኩል አሟልጮ ለመግባት እንዲያስችል !!"

ቅልጥልጥ ያለን ውሸት ነጋ ጠባ እየደገሙ፤ስደት ለወሬ ያመቻልና ነፍሰ ገዳዮቹ ሰለባ ነን ብለው እየለፈፉ፤ትላንት የወጉትን ወይም ሲታገል ቅንጣት ድጋፍ ያለሰጡትን ዛሬም ዓይናቸውን በጨው አጥበው ሲዘምቱበት ማየታችንን በኢሕአፓ ላይ እየደረሰ ያለው የሀሰት ናዳ ምስክር ይሆናል ። ወያኔ ስልጣኑን ለመጠበቅ ያሰጋኛል ብሎ ከልብ የሚፈራውን ድርጅት ባገኘው ቀዳዳ ሁሉ ለማጥቃት መነሳቱ የሚጠበቅ ሲሆን ይህን ዘመቻ አጅበው በድርጅቱ ላይ መሠረተ ቢስ ክሶችንና አሳፋሪ ውሸቶችን የሚረጬት ግን በጥብቅ መወገዝ ያለባቸው ናቸው ። ኢሕአፓ የኢርትራን መገነጠል ወይ ነጻ መሆን አልቀበል ብሎ ከሻዕቢያ መጣላቱና በዚህም መጎዳቱን ደግሞ ደጋግሞ የገለጸ ሲሆን በመሰረቱ የዚህን ትክክልነት ኢሳያስ አፈወርቂ ሳይቀር አረጋግጦታል ። ለዚህም ነው ድርጅቱ ኤርትራን አስገነጠለ የሚለው ክስ ከንቱ ሆኖ 'ትል የሞላው ቋንጣ ሆኖ አሁንም ሊለፍፉት የሚጥሩ ማፈሪያዎችን መስማቱ የሚያንገሸግሽ የሆነው ። በቅርቡ ጊዘ ወደ አሜሪካ ተጉዞ በዚያ ትውልድና በኢሕ አፓ ላይ ጸያፍ ዘመቻ የከፈተው የቆሻሻ ታሪክ ባለቤት ፕሮፌሰር እንጂ ደርግ 60 ዎቹ ላይ ላደረሰው ግድያ ኢሕ አፓ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም ። የአሜሪካ መሳሪያ ሆኖ አልተገኘም ። የደርግ ኢሰፓ ባለስልጣን ሆኖ ግፍ በሕዝብ ላይ አልፈጸመም ። በአሶሳ ሻዕቢያና አነግ አማራውን ሲገድሉ ዝም አላለም፤አወገዝ አጋለጠ እንጂ ። በከተማ በገጠር ደሙን ለሀገሩ አፈሰሰ እንጂ በደርግ ለነጻ ትምህርት በየኩባና ምስራቅ አውሮጳ አልተላከም ። ኢሕአፓ ለሀቅ ቆመ እንጂ በሬ ወለደ፤ በመውለድ ላይ ነው ይወልዳልም ከሚሉ ነፍሰ ገዳዮችና አረመኔ አገዛዞች ጋር አልሰመረም፤አላበረም ። ምናልባትም ይህ ይሆናል አላቋርጥ ላለው የሀሰት ዘመቻ ምክንያት የሆነው ።

## የተዳፈነ እሳት የጠፋ ይመስላል::
## በኢሕአፓ ላይ ዘመቻው ተጧጧፈሳ!

**ክፍል 2**

"ተፈጥሮ ሥርዓቱን ካልቀየረ በቀር
የህላዌ ኪደት ካልዋጠው ውዝንብር
ካላበደ በቀር ህሊናው ካልዛለ
ከቶ ማነው ደፍሮ "እሳት ጠፋ" ያለ?"
ሀይሉ ገሞራው (ሀ. ገ. ዮሐንስ)

እሳት ቢዳፈን የጠፋ ይመስላል የተባለውን የዘነጉ ኢሕአፓ ጠፋ ተነነ ሲሉ ዓመታት አልፈዋል። ይህ ምኞት-ቅዠታቸው እውን የሚሆንበት ጊዜ ከኮከብ ርቆ በመገኘቱ ቀቢጸ ተስፋ ይህን ጎራ ወሮ ይወዘውዘዋል። ኢሕአፓ ግን አለ። ለድርጅቱ ህልውና ምክንያት የሆኑት መሰረታዊ የህብረተሰቡ ቅራኔዎች አልተወገዱምና መኖሩን ወደ አለመኖር ሊቀይር የሚችል ሀይል ወይም ሁኔታ እስካሁን አልተከሰተም።
ሳይሞከር ቀርቶ አይደለም። ነጻ እርምጃና ቀይ ሽብርን ያስታውሷል። የህዝብ ጠላትና ፋሺስታዊ ደርጎች ነጋ ጠባ ኢሕአፓ የ "ሰላሙን" ሁኔታ በራሱ ቀይሮ ተኩስ ከፈተና ደርግን "ቆሰቆሰው" ሲሉ ቢደመጡም (የቅርቡ አቅራሪ ደግሞ ያ ፍስሃ ደስታ ይባል የነበረው ፋሺስታዊ መኮንን ነው ) ሀቁ ግን ሌላ መሆኑን ደግመን ደጋግመን ያስረዳነው ነው። የፋሺስቶቹ የገደል ማሚቴዎችም ነጭ ሽብር ገለመሌ እያሉ ቢጮሁም ኢሕአፓ ለደርግና አጋሮቹ ጥቃት ከተጋለጠ ከብዙ ጊዜ በኋላ የመከላከል እርምጃዎችን መጀመሩን ታሪክ መዝግቦታልና ይህን ፍቆ ሀሰትን ለማስፈን የሚቻል አይደለም። ፍስሐ ደስታ ቀደም አለቆቹ መንግስቱና ፍቅረስላሴ ባሳተሙበት የደርግ ስንክሳር ጠራቂ ተቋም ተረድቶ ባሳተመው መጽሃፍ ብዙ ደርጋዊ ቅጥፈቶችን ሕይወት ሰጥቶ ሲያቀርብ ሊያጋልጥ የሚገባውን ሀቅ ግን ዘነጋሁት ዓይነት ብሎ ማለፉን የመረጠ ይመስላል። ሙሉ ትችት ጊዜውን ይጠብቅና ወደቁም ነገራችን እንመለስ። ውሸት ለምን? ውሸት እንዴት?

ሀይሉ ገሞራው እንዲህ ብሎ ነበር፤

*" ባብዛኛዎቻችን ዘንድ እንደሚታወቀው በነገረ-ምንታዊ አስተሳሰብና አመለካከት (ዱዋሊዝም) መሰረት ውሸት ወይም ሐሰት ወይም ቅጥፈት በመሰረተ ባሕርዩ የትልቁ እውነት አንጻራዊ ምንዝር ነው። እንደታመነበት ሁሉ በተፈጥሮው ህልው ለሆነ ነገር ሁሉ፡ በትይዩ ገጻዊ ጣምርነት የተቀየዱ የባለመንታ ባህርያት ኩነቶች ይንጸባረቁበታል። በሐሳባዊ መዋቅራቸውም አንጻር እያንዳንዱ ህልው የጽራሬታዊ ንጻሬ አፍራሻዊ ቅንብር ውጤት ነው። ይህ ስሪታቸው እንደሚያሳየው ከሆነ ማንኛውም የዓለማችን ህልው ነገር ንጻሬያዊ አጣማጅ ያለውና ምንነቱንም ለመተርጎም አንዱን ከሌላው ጋር አገናዝቦ ማረብ ወሳኝ እንደሚሆን ተረጋግጧል። ይህም ማለት ማንኛውም ነገር የብቸኝነት ባህርይ ቢታይበትም ቅሉ ምንነቱን ሰቅስቆ ለመረዳት በነጠላነቱ ብቻ በጉልህ ሊታይና በሥርዓት ሲገለጽ አለመቻሉንና ቢሞከርም እንኳን አርኪና አመርቂ ውጤት አያስገኝም ማለት ነው። .... ስለ ውሸት ማንነት የሚናገር ሁሉ በአንጻሩ እውነት እንዳለ ያውቃል። ለመሆኑ ውሸት (ሐሰት) በመሰረተ ባህርይዋ ምንድር ናት? የሚጠቀሙባትስ ምን ዓይነት ዝንባሌ ያላቸው ሰዎች ናቸው? ....*

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

ከገጽ 6 የዞረ

“እንግዲህ እዚህ ላይ የውሸትን ትርጉም ማስጣት ይቻላል። ውሸት ሐሰት ወይም ቅጥፈት በመሰረቱ በመንፈስ የደከሙ ሰዎች፤ ራሳቸውን ብቻ ለመጠበቅና ለማዳን፤ በበላ ባይነት ስሜት የሚንሻፈፉ ወራዳዎች የሚጠቀሙበት የማታለያ ዘዴ ነው። ስለሆነም ከሞራል፤ ከኤቲክና ከተራ የዕውነት ዲሲፕሊን አፈንግጠው በወጡ ሰፍሳፋ ሰዎች በየዕለቱና በያጋጣሚው የሚፈጸምና የሚከወን የተራ ብልግና ምናብ ነው። በሥነ ልቦና ጥናት እንደተደረሰበት ከሆነ ደግሞ የራስን ፍጹም መውደድን ብሎም ስለ ግል እኔነት ብቻ ከሚያስብ ህሊና የሚፈነጠቅ የሰዎች ሞራላዊ ድክመት ርጭት ነው። በመሆኑም ‘ፍቅረ ርዕስ’ ጎልቶ የሚታይባቸው፤ የባሰ ‘እበላ ባይ ሰዎች’ ኢሞራላዊ ህሊና ነጽብራቅ ነው። ከእንዲህ ዓይነት ሰዎች የሚመረት ውሸታዊ ምርት በባህርዩ ጸረ ሐቅና ጸረ ሞራል ነው። ሐሰት በዚህ ትርጉሙ የመተማመን፤የመከባበር፤ የመወዳጀት፤ የመፈቃቀር፤ የመተሳሰብና የመሳሰሉትም በጎ ባሕርያት ጸርና ተቃራኒ መሆኑ ግልጽ ነው። በርቱዕ ይሁን በኢርቱዕ፤ በጠቅላላው የበጎ ስነ ምግባራት አባላት ሁሉ ደመኛ ጠላት መሆኑም ይታወቃል። ውሸትም እንደፈለገው ተዘርሮ ለመተኛት የእንጭጭ ህሊናዎች አልጋነት ይመቸዋል። በተለይም በጥራዝ ነጠቅነት የሚመጻደቅ የልሳን ምሁር ነኝ ባይ ባጋጠመው ወቅት፤ ተንኮለኛው ውሸት አንዴ ተጣብቆ እስከ መጨረሻው አይለቀውም። ‘የጊዮርግስን መገበሪያ የበላ…’ እንዲሉ። እንደዚያው ዓይነቱ ሰው ለአያ ውሸት መንደላቀቂያ ሶፋው ነው::"

ይህ በገሞራው ከዓመታት በፊት የተጻፈ ትችትና ማብራሪያ ዛሬ ያሉትን ጸረ ኢሕአፓ ዋሾዎች አሳምሮ ይገልጣቸዋል። ያ ኢሕአፓን ከወለደው ጀግና ትውልድ በፊት የነበሩና በህይወት ካሉት ምሁሮች አንዳንዶቹ የዚያን ጊዜ ክስረታቸው ምስክር ይህ ድርጅት ነውና መኖሩን መባጀቱን ከቶም አይፈልጉትም። እንኳን ንጉሱን ይማጠኑ የነበሩት ቀርቶ ተራማጅ ነን ብለው ሊመጻደቁ የጣሩትም ቁርጥ ቀን (ያውም ለስለስ ብላ)ስትመጣ ሸብረክ ማለታቸውን ያ ትውልድ ታዝቧልና አይወዱትም። ሕዝቡ አልነቃም፤ ገና ሁለት ትውልድ አልፎ ምናልባት ይነቃ ይሆናል እያሉ ሲዳዱም የነበሩትን ሕዝብን አደራጅቶ ታሪክ የማይረሳው ትግል አስተባብሮ በማታገሉ ህያው ምስክር ነው ለክስረታቸው፤ ለባዶነታቸው:: ስህተታቸውን የተቀበሉ ሲኖሩ ሌሎቹ ደግሞ በቂመኝነት ትውልዱ ላይ እስካሁን ይዘምታሉ። ዋሾዎች የሀቅን ምስክሮች ሊወዱ አይጠበቅም። ከነዚህ ብኩኖች አንዱ ለንጹህ ዜጎች መገደል ሁሉ ቢያንስ በሁለት አገዛዞች ተጠያቂ ሆኖ ሳለ ዛሬም መድረክ ይዞ ያን ትውልድ የሚወነጅለውና በተለይም ኢሕአፓ ላይ ያነጣጠረ ዘመቻ አጃቢ የሆነው ለዚህ ነው። ሀይሉ ገሞራው ግዜ ፈጅቶ ስለ ውሸት የጻፈው ውሸት ሀገር አጥፊና ትግልንም አደናቃፊ መሆኑን ጠንቆቅ በማወቁ ነው።

በኢሕአፓ ላይ በየአቅጣጫው የተከፈተው ጻያፍ የሀሰት ዘመቻ የሚያሳየው ይህ ድርጅት ቅዠታቸው መሆኑንና ያደናቅፈናል ብለው ስጋት እንዳላቸውም ነው:: ርኩስ ትብብር በደርግም በወያኔም ሊፈጠር የቻለውና ይህንንም ባዕዳን ደጋፊ ሆነው የተገኙት አለምክንያት አይደለም። ቀደም ደርግ ወያኔን አስታጥቆ ኢሕአፓና ኢዲህን ሊያስጠቃ ሲፈራገጥ ዋና ባለጉዳይ የነበረው ፍስሐ ደስታ (ወደ ወያኔ ጠቅሎም ሊከዳ በሚል ሶስት ጊዜ በምስጢር ከወያኔ ጋር መገናኘቱን መለስ ዜናዊ ራሱ መናገሩን መስካሪዎች አሉ) ባይገልጸውም ደርጎችና ወያኔዎች ሲያብሩ የመጀመሪያቸው አይደለም። ይህንንም በስፋት የምንመለስበት ይሆናል--መረጃው በእጅ ነውና። የፋሺስቶችን ወንጀል በተናጠልም ሆነ በጋራ፤ ኢትዮጵያን ሉዓላዊነቷን በሚያሳጣ መንገድ ለፈረንጅ ያደሩትን፤ ጉዳት በሕዝብ ላይ ያደረሱትን ሁሉ የታገላቸውና የሚያውቃቸው ይህ ድርጅት በመሆኑ በጠላትነት በነሱ ተፈርጆ መጠቃቱ ለእነሱና ለጌቶቻቸው ወሳኝ ጉዳይ ነው። በኢሕአፓ ሰራዊት ላይ የብተና አደጋ ሲደርስ ይህን በመጠቀም ድርጅቱ እንዳያንሰራራ ማድረግ ይገባል ይቻላል በሚል እነ ሚቹ ደረጃ ደሬሳ ያስገቡት ማመልከቻ በዚህ መሰረትም ሲአዬ- አሜሪካ (በሱዳን ተባባሪነት) የወሰዱትን እርምጃ የምንረሳው አይደለም። ይህ ሙከራቸው ከሸፎ ድርጅቱ ሲቋቋምና ሰራዊቱም በአዲስ ሲጠናከር በድንገት ለመምታት ሱዳን-አሜሪካና ሻዕቢያ ተባብረው በጦር በጭልጋ በቋራ ሊያጠቁት ሞክረው ድባቅ መመታቸውም የሚታወስ ነው። ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ነውና፤ መቼም ቢሆን መቼ ለሱዳኑም፤ ለአሜሪካም ሀገርን አልሰጥ ብሏልና፤ ከሻዕቢያ ሸበጥ/ጫማ ስር ወድቆ አልተዋረደምና ሁሉም እንዲጠፋ የሚረባረቡበት ጠላት ሆኖ ቆይቷል። ዛሬም የተለውጠ ቅንጣት ነገር የለም ። ብዙ መቶ ሺ ዶላር እየፈሰሰ ያለውም ይህንኑ ርኩስ ተልዕኮ ከግብ ለማድረስ ነው። ይህ ሁኔታም ድርጅቱን ሊያኮራው የሚገባ ነው። ትግል ጀምረው ከፈረሱት ወይም ከመጀመሪያው ሕዝብን ጥለው ከጠላት ከተሰለፉት ባለመሆኑ፤ ቃልኪዳኑን ባለመካዱ፤በጽናት በመቀጠሉምና ዛሬም ለህዝብ ጠላቶች ቅዠትና መቅሰፍታቸው ሆኖ በመገኘቱ።

ወደ ገሞራው ስንመለስ ደግሞ የሚከተለውን ቁም ነገር እናነባለን፤

*" ዕቅጪን ተናግሮ ከመሸበት ያድሯል ብለው ሲናገሩ ኢትዮጵያዊ ብሂልነቱ ካንጀት ነው። ከዚህ አባባል ሐቀኛነት የተነሳ ብዙ ጊዜ ብሒሉን የሚጠቀሙበት ስለ አንድ ጉዳይ እውነትነት ከተናገሩ በኋላ እንደ ማሳረጊያ አድርገው በመሐላነት ደረጃ ነው። የሐቅን ክብርና የሐሰትን ክስረት ለማስረዳትና በየትውልዱ ዘመን በከፍተኛ ጥንቃቄም ለማስተማር የቀድሞዎቹ ብዙ ተናግረዋል ። ከነዚሁ ብሂሎቻቸው ውስጥ፤*

እውነት ያድናል ውሸት ግን ይገድላል
ውሸት ይዳርጋል ለሞት
ውሸትንና ቅራሬን ሽምጥጥ ነው
ውሸታም ሰው ማስታወሻው ጣቃ ነው
የዋሾን ክፉ እሳት በአፉ
ከከብት ቀበኛው ከሰው ወሬኛው
ዘባራቂ ይወዳል መራቂ

የመሳሰሉት በብዛት ይገኛሉ። የኢትዮጵያዊው የፍትህ፤ የፍርድና የርትዕ ተቋሞች ሁሉም መሰረተ-ሕንጻቸው የቆመው የውሸትን ቅጥፈታዊ ባህርይ በማጋለጥና ተገቢ የቅጣት ዋጋውን ለመስጠት ነው። በመሆኑም የባህላችን አከርካሪ አጥንት የእውነትንና የሐቅን ሕልውና እንደ አምድና ምሰሶ ደግፎ እንዲኖር የተዋቀረ ስሪት ነበረው። ይሁን እንጂ በፍርድ ቤቶች መድረክ ላይ በየጊዜው የሚፈሉ ውሸት በቀል ዳኞች የእውነትን ፍትሐዊ መንገኒቅ በሙስና (ጉቦ-ቦቅስ) እየጠመዘዙ፤ ለውሸትና ለሀሰት የመኖር ዕድል ሲሰጡ ኖረዋል። ይህም ኢፍትሓዊ ተግባራቸው በማህብረሰባችን አባልት ላይ ተጽዕኖ በማድረጉ የነገረ ሀሰት ዘር በየትውልድ መካከል ሲሰራጭና ሲራባ ለመኖር ምክንያት ሆነ። ዛሬም በተለያየ መልኩ በልዩ ልዩ የህብረተ-ሰብ ክፍሎች ውስጥ ነገረ ሐሰት እንዳንሰራራ አለ።"

ውሸት ማንሰራራት ሳይሆን አልፎለት ነግሶብናል ማለቱ ተገቢ ነው። ቢያንስ የደርግና የወያኔ አገዛዘ ስረ መሰረታቸው ውሸትና ቅጥፈት ነው። ደርግ ትውልድን ፈጅቶና መትሮ ሀገሪቷን ለወያኔ አመቻችቶ ሲያስተላልፍ የዜጎችን ባህል፤ ስነስርአትና ቆራጥነትን አዳክሞ ነው። ፍርሃትን አንግሶ:: ይህን አመቺ ሁኔታ የተረከበው ወያኔ ደግሞ ጎጠኝነትን (ዛሬ ተቃዋሚ በሉን በሚሉት ሙሉ ድጋፍ) አከለበትና፤ ወያኔን ልጆቼ በሚሉት ታገዘና ህዝብን ከፋፈለው። አልባሌ ልምዶችንም አሰራጨ፤ ግለኝነት መረንና ልክ አጣ፤ ከሀገር በፊት ሆድ አብጦ አለሁ አለ። ውሸት ቪላዋን ሰራችብን። ሀቅ ተናጋሪዎችና ለሀገር የሚቆሙ ውጉዝ ከመ አርዮስ ተባሉ። ስንቶቹ ጀግኖች በደም የጻፉት አኩሪ ታሪክ ተፍቆ ከሀዲና ባንዳዎች፤ ሆዳሞች ጠባቦች፤ ቀጣፊዎች በሞላ መድረክ ላይ ሊርመሰመሱ ቻሉ። ይባስ ብለው አርበኞቻችንን ለጣሊያን ያደሩ ብለው በአደባባይ ሊያወግዙ ለፈሪዎቹ ተፈቀደላቸው። እንደሚታየው ኩይሳ እንኳን የማይሰራ ከንቱ የምስጥ ክምችት ነው ዛሬ በኢሕአፓ ላይ እየዘመተ ያለው። ሀገሩን ሊያጠፉ ሲባዝኑ ከቆዩት ጋር አብሮ በኢትዮጵያ ላይ የተነሳው። እስቲ ዛሬ በፖለቲካው መድረክ ያዙን ልቀቁን ባዮችን እንዘርዝርና ታሪካቸውን ለመመርመር እንነሳ-- ሀሰቱ፤ ማደናገሪያው ተኖ ሀቁን ካበራየነው ማንነታቸውን ማለትም ጸረ ኢትዮጵያነታቸውን በግልጽ እናያለን።

" ይዳፈናል እንጂ መች ይጠፋል እሳት
መፋፋም ቅራኔው ገንፍሎ እስኪወጣ
በዚያች የሀቅ ዕለት።
በግለት ፈንድቶ ከተዳፈነበት ሲወጣ አደባባይ
ያን ዕለት ይሆናል ከጭድ ጋር ጋብቻው
ሀይሎጋ የሚያሳይ።
ባይገባው ነው እንጂ የእሳት ተፈጥሮ
ከእሱ ሞት በኋላ ይኖራል ሲያቃጥል የፋሺስት ጭራሮ
እንዴት ቢደፍር ነው
የሚል በአደባባይ አጥፍቻለሁ እሳት
ካላወቀ በቀር ወይም ካለማወቅ የእኛ ደበብ ፋሺስት ።"

ከኢሕአፓ አንጻር የሚከተለውን ጫና ሰጥተን ማቅረብ እንፈልጋለን፤

- ትላንት ተመስርቶ ነገ ተነገ ወዲያ ያልጠፋ ድርጅት ኢሕአፓ ነው--ያውም ስንት ጥቃት ደርሶበት። 44 አመት ትግል ቁጥር ድርደራ ሳይሆን የጽናትነት ምስክር ነው።
- በኢትዮጵያውያን ጀግና ዜጎችና ተራማጅ ወጣቶች የተደራጀ ድርጅት ኢሕአፓ ነው።
- ማንም ባዕድ ይህን ድርጅት አልመሰረተውም አላዘዘውም፤ትላንትም ዛሬም።
- ኢሕአፓ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማንም አሳልፎ አልሰጠም፤ ባለመስጠቱም መከራን መቀበል ግድ ሆኖበታል።
- ኢሕአፓ ቤተ እስራኤሎችን በተመለከተ ህዝብን በገንዘብ አልለወጠም፤ የገንዘብ ጥቅምንም ከጭቁኖች ውጥረትሊያገኝ አልጣረም። ድልድይ ለሱዳን ሲል አላፈረሰም። ሱዳን ስለጠየቀው የደቡብ ሱዳን ስደተኞችን አሳልፎ አልሰጠም። ሱዳን መንግሥት ነው ብሎም ቋራን አሳልፎ አልሰጠም። ቻይና መከረኝ ብሎ አልተጎነበሰም። ወዘተ የወያኔ ታሪክ ግን የዚህ ተጻራሪ ነው። ሁሌም ክህደት፤ ሁሌም ጸረ ኢትዮጵያነት።
- ኢሕአፓ ከሕዝብ ጠላቶች ጋር አላበረም፤ ስልጣን አልተካፈለም፤ ቃል ኪዳኑን አልካደም።
- ኢሕአፓ እንዲያውም ከልክ ባለፈ ለቀቅተኛ ተባለ እንጂ የተቃወመውን በዚህ ምክንያት የተነሳ አልገደለም።
- ለዚያድ ባሬ፤ለገዳፊና ለሻዕቢያ መቸም አልተጎነበሰም። ትላንትም ዛሬ ድርጅታዊ ነጻነቱንና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት አሳልፎ አልሰጠም።
- አሜሪካም ሆነ ሱዳን፤ ሻዕቢያም ሆነ ግብጽ፤ እንግሊዝም ሆነ ፈረንሳይ ትላንትም ዛሬም ኢትዮጵያን በሚጎዳ ደረጃ ተሰለፍልን ሲሉት መልሱ እምቢኝ እንጂ እሺ ሀገር ልሸጥ ሆኖ አያውቅም።

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ከገጽ 7 የዞረ

- በደርግም በወያኔም ጊዜ በህዝብ ላይ የሚደርሰውን በደል ተቃወመ አጋለጠ እንጂ የደርግ ካድሬና ባለስልጣን፤ አማካሪና ንግግር ጻፊ፤ ወዘተ ሆኖ ራሱን አላዋረደም። ሽብር፤ በግድ መንደር ምስረታ፤ አሶሳ፤ በደኖ፤ አርባጉጉ፤ አሰቦት፤ ምስራቅ ወለጋ፤ ጣና በለስ፤ ጋምቤላ፤ኢጋዴን ወዘተ--የመጀመሪያው ጯሂና ተቃዋሚ ኢሕአፓ እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል። ሌሎችስ የት ነበሩ? እስቲ ድማጻችን ተሰማ፤ ተቃውመን ነበር ሊሉ የሚደፍሩትን እንስማቸው!

በትግል የሚሰማራ ማንኛውም ድርጅት -- በተለይም የድርጅታዊ ትግል ተመክሮ ብዙ ባልሆነበት-- ስህተት ሊፈጽም መቻሉ የሚጠበቅ ነው። ኢሕአፓ ስህተት ብሎ ያመነባቸውን በግልጽ አውጥቶ አሳውቋል። ጭቆናን በመታገሉ ግን ቅሬታም የለውም፤ ማንንም ይቅርታም አይጠይቅም። ከአረመኔው ደርግ አብረው የቆዩና ወደዱም ጠሉ የወንጀሉ ተባባሪ የነበሩ፤ ወያኔ ለስልጣን ሲገባም ያጨበጨቡና አብረውት በበደሉ ፍርፋሪው የደረሳቸውና ለመለስ የሰገዱት ወይም ዋና ወያኔ የነበሩት፤ ሕዝብ ሲፈጅ ሲወገር ድማጻቸው ሳይሰማ ዓመታት ያለፈና መሰሎቻቸው ዛሬ ገልበጥ ብለው ኢሕአፓን ሊከሱ ሊወነጅሉ ቢነሱ፤ ቢዋሹ ቢቀጥፉ ሀቅን ሊቀብሯት የሚችሉ አይደለም። ኢሕአፓም ሲገፋ መከላከልን በተመለከተ ግዴታው ሲሆን ተመክሮም አለውና ሂደቱና ውጤቱ ለዋሾዎቹ አመቺ እንደማይሆን ግልጽ ነው።

ባልተናገሩ ባላፈሩ ነው። ታሪክ የተረሳ መስሏቸው በኢሕአፓ ላይ በወያኔ የታጀበ ዘመቻ የከፈቱት ሁሉ ማፈራቸው ገና መጀመሩ ነው። ወያኔ ላይ እናተኩር በሚል ቅኝት ለመመራት ብንጥርም ጥቃት ሲበዛ፤ የሰማዕታት ስምና ታሪክ በዝቃጮች ሲጠቃ ዝም ብለን የመቀበል ልምዱ የለንምና ሁሉም የኢሕአፓ አባልና ደጋፊ በያለበት/ባለችበት ድርጅቱን እንዲከለላከሉ መጥራቱ አስፈላጊ ሆኗል። መከላከል በሁሉም መስክ፤ ባለምንም ቸልተኛነት።

ይህም ጽሁፍ ይህን ግዳጅ ሊያሟላ ቀጣይ ይሆናል።

ይቀጥላል ።.............................

## በዲሲና አካባቢው ካሉ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

ጥቅምት 2008 ዓ.ም.

## የተከፋፈለ መጠቃቱ አይቀሬ ነዉ

እንደሚታወቀዉ ድርጅታችን ኢሕአፓ የታገለለትና ብዙ ዋጋ የከፈለለት አሁንም የሚታገልለትና የሚከፍለልት ኢትዮጵያዊዉ በዉጪም በዉስጥም አንድነቱን ጠብቆ እንዲኖር ነዉ።

ትላንትም ሆነ ዛሬ፣ ነገም ሆነ ወደፊትም ድርጅታችን ኢሕአፓ በሃይማኖት ዉስጥ ጣልቃ አልገባም፤ አይገባምም። ለዚህም ነዉ በተለይ ባለፉት 24 ዓመታት በስልጣን ላይ የተቆናጠጠዉ የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክህነት ሆነ በኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖት ዉስጥ ፈርፍሮ ገብቶ በቅድሚያ በሲኖዶሱ አሁን ደግሞ በመጅሊሱ ላይ ሲያካሄድ የቆየውን የመጠቅለል ተግባር በፅኑ የምንቃወመዉ።

አንደሚታወቅዉ በህዝብ የተቋቋሙና የሕዝብ ንብረት የሆኑ ተቋሚትን አብያተ ክርስትያናትን ጨምሮ ወያኔ በቁጥጥር ለማስገባት የሚያደርገዉን እንቅስቃሴ ህብረተሰቡ ጠንቅቆ አንዲጠብቅ ስናስጠነቅቅ ባጅተናል። እነሆ በዋሽንግተን ዲሲ ቀዳሚ በተክርሲቲያን አንዱ በሆነችዉ በደብረሰላም ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ሠሞኑን እየታዩ ያሉት አስደንጋጭና አሳዛኘ ድርጊቶች እንደ አንድ ሃላፊነት እንዳለዉ ሃገራዊ ድርጅት በጥሞና እየከታተልነዉ እንገኛለን።

ከመጀመሪያዉ በዉይይትና በህግ ደንብ መሠረት ሊፈቱ የሚችሉ ቀላል ጉዳዮች ተለጥጠዉ እዚህ በመድረሳቸዉ የተሰማንን ሀዘኔታ እየገለጥን፣ ከዋናዉ ጉዳይ አዉጥተዉ በየዋህነት በተታለሉ ሆነ በፀረኢሕአፓ ግለሰቦች የሚናፈሰዉን አሉባልታ በከፍተኛ ደረጃ እናወግዛለን። ከነገረቀደም ኢሕአፓ ማለት ከሠማይ የተንጠባጠበ ምትሃታዊ ሃይል ሣይሆን ኢትዮጵያዊ ልጆች ያቋቋሙት ዘርና ሃይማኖት ሣይለያቸዉ ለሀገር የሚታገሉበት ድርጅት መሆኑ መታወቅ አለበት። አባላቱ ከተለያየ ዘር የተሠበሠቡ አንደመሆኑ መጠን የተለያየ ሃይማኖት አማኞችም ናቸዉና አንደየ እምነታቸዉ፤ አምነታቸዉን ጠብቀዉ ባሻቸዉ ቤተ እምነት የመሄድና የመሣተፍ መብታቸዉ የተጠበቀ መሆኑን አስረግጠን ለማሳወቅ እንወዳለን።

ወደ ቁም ነገሩ ስንመለስ ሠሞኑን የተካሄደዉና እየተካሄደ ባለዉ በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ችግር ዉስጥ ኢሕአፓ አለበት የሚባለው ወሬ መሰረተ ቢስ መሆኑን በአጽንኦት እየገለጽን እንደሚወራዉ አንድም የኢሕአፓ አባል በቦርዱ ዉስጥ በአባልነት የሌለበት መሆኑን ግልጽ ማድረግ እንወዳለን። ቢኖር ኖሮ አለ ለማለት የምናፍርበት ወይም የምንፈራው ምድራዊ ሃይል የለም።

መግለጫችንንም ስንቋጭ ፣ የቤተክርስትያኗ ችግር ሊፈታ የሚችለዉ በውይይትና በአባላቱ የተሳትፎ ዉሳኔ፤ እንዲሁም በዕርቅ ነው እንላለን። ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርነዉ የተከፋፈለ መጠቃቱ አይቀሬ ነውና ወያኔ የተባለ ተምች በግርግር ገብቶ ቅራኔ አባብሦ ቤተ ክርሲቲያኗንም ሆነ ሌላ ኢትዮጵያዊ ተቋማትን እንዳይወር አጥብቀን እንደምንከላከልና ምዕመኑም ይህን ተገንዝቦ በስርዓት ያሻዉን የመወሰን መብቱ የተጠበቀ ነዉ እንላለን።

በመጨረሻም በፀረ ኢትዮጵያዉ ወያኔ ና በኢሕአፓ መካከል ያለዉ የማይታረቅ ቅራኔ ሥለሆነ ኢሕአፓ በማይመለከተው የሚቀርብበት ክስ እንዱ በራሱ በወያኔ ሌላዉ ደግሞ ኢሕአፓን ማጥፋት ማለት ወጣቱን በጅምላ ጨፍጭፎ ሬሣ መራመድ ነዉ ሲሉ በነበሩ የመንግስቱ ሃ/ማርያም አንጋሽና አንጋች ካድሬዎችና አብዮት ጠባቂዎች ነው። ዛሬ ያለንሰሃም ቢሆን (የቤ/ክርሲቲያኗ አባል ወይም መጠምጠም መብታቸዉ ቢሆንም) የራሳቸዉን ቁርሾ ለመወጣት በኢሕአፓ ላይ የሚያደርጉትን ዘመቻ ህብረተሰቡ እንዳይቀበለዉ በትህትና እንገልፃልን

ኢሕአፓን ለቀቅ!!
ወያኔን ጠበቅ!!

**ጥያቄ ወይም አስተያየት ካላቹ በኢሜል dc.region.eprp@gmail.com፣ በስልክ ቁጥር (202) 291-4217 ወይም በቢሮአችን 5309 Georgia Ave. NW Washington DC. ድረስ በመምጣት መገናኘት ይቻላል።**


የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ በኢትዮጵያ እና በጎረቤት አገሮች ለሚገኙ አድማጮቹ በናይልሳት ከመስከረም 24 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ በአዲስ መስመር ስርጩቱን የጀመረ መሆኑን ለአድማጮቹ በደስታ ይገልጻል። ስርጭቱ በሚከተለው የሳተላይት መስመር ይተላለፋል።

Satellite : Nilesat
Azimuth : 7/8 deg West
Frequency : 12.604 MHz
Polarisation : Horizontal
Symbol rate : 27500
FEC : 5/6
Channel Name : Finote Democracy

